# - ዘ -

ዘመኑ ግልምቢጥ ፣ ውሻ ወደ ስርዶ አህያ ወደ ሊጥ ።

ዘመን የሰጠው ቅል ፣ ድንጋይ ይሰብራል ።

ዘመን የወለደው ፣ ንጉስ የወደደው ።

ዘመደ ብዙ ጠላው ቀጭን ነው ።

ዘመዱን ያማ ፣ ገማ ።

ዘመድ ሲጣላ ያረክሳል

ዘመድ በዘመዱ ፣ አይጨክንም ሆዱ ።

ዘመድ ቢረዳዳ ፣ ችግርም አይጎዳ ።

ዘመድ ከዘመዱ ፣ አህያ ካመዱ ፣።

ዘመድ ያረጀ ፣ በልቶ ያፈጀ ።

ዘመድና መድሃኒት ፣ የተቸገሩ ለት ።

ዘመድና ሚዛን ከወገብ ይይዛል ።

ዘመድና እሳት ሩቅ በሩቅ ።

ዘመድና ዋንጫ እያለቀሰ ይመጣ ።

ዘመድና ገንዘብ ሳያስቡት ይገኛል ።

ዘመድና ፍየል ቤት አጥፊ ነው ።

ዘመድን ከዘመድ ጋር ማማት ፣ ዳቦ መጣመጥ ነው ።

ዘመድን የሚወጉበት ጦር ጀንፎው አይለቀቅም ።

ዘምቶ ተወረሰ ።

ዘምቶ ያረጀ ፣ በልቶ ያፈጀ ።

ዘረፋና ቀን ካልተሻሙበት ያልቃል ።

ዘሩ የጣቴ ፣ ምድሩ ያባቴ ።

ዘር ልትበደር ሂዳ ፣ እህል ሲሸት መጣች ።

ዘር ከልጓም ይስባል ።

ዘር ከልጓም ይጠቅሳል ።

ዘርቶ መቃም ፣ ወልዶ መሳም ።

ዘርቶ ያልበላ ፣ አምላክን ጠላ ።

ዘንጋዳ ተቀረጡት አገዳ ፣ ሚስት ከፈቷት ባዳ ።

ዘንጋዳ ተቀረጡት አገዳ ፣ እደኛ ከደረሱ እዳ ።

ዘንጋዳ የገለበጠ ፣ አባቱን የገላመጠ ።

ዘንጋዳና ወታደር ፣ በመከር ጊዜ ይታይ ነበር ።

ዘንዶ ፣ የዳገት በረዶ ።

ዘንግ ከተተከለ ልብ ተከፈለ ።

ዘኬውን ሲቋጥር ፣ አነቀው ነብር ።

ዘጠኝ ሞት መጣ ቢለው ፣ አንዱን ግባ በለው አለው ።

ዘጠኝ ጠጥቶ አስረኛውን የወደደ ፣ በሙሉ ነደደ ።

ዘጠኝ ጠጥቶ አስር የወደደ ፣ ዘጠኙ ተናደ ።

ዘፈን በበገና ፣ ነገር በዋና ።

ዘፈን በከበሮ ፣ አዋጅ በደበሎ ።

ዘፈን አለ በገና ፣ ነገር አለ በዋና ።

ዘፍኖ አያምር ፣ እንኳን አልቅሶ ።

ዘጥ ዘጥ ፣ አቁማዳ ቂጥ ።

ዛር ልመና ፡ ሳይያዙ ገና ፤ ከተያዙ ብዙ ነው መዘዙ ።

ዛብ የሌለው ፈረሰኛ ፡ ምሳ የሌለው ኮሶኛ ።

ዛፍ ሲወድቅ ከግንዱ ፡ ሰው ሲቸገር ከዘመዱ ።

ዛፍ በሌለበት እንቧጮ አድባር ይሆናል ።

ዛፍ ዝናብ ያስጥላል ፡ ትልቅ ሰው ከዳ ያስጥላል ።

ዛፍ ያለቅርንጫፍ አይደምቅም ፡ ሰው ያለሰው አይከበርም ።

ዛፎች ቢጠፉ ፡ ቁጥቋጦች ተሰለፉ ።

ዜማ በሃሌ ፡ ነገር በምሳሌ ።

ዝሆኑ ሳለ ዱካውን ።

ዝሆን ለቀንድ ፡ ባላባት ለትውልድ ።

ዝሆን ቂጡን ተማምኖ ግንድ ይውጣል ።

ዝሆን እንሆት ፡ ፍለጋው ወዬት ።

ዝሆን ጥርሱን ፡ አዝመራ ገብሱን ።

ዝም ማለት ከሞኝ ያስቆጥራል ።

ዝም ባለ አፍ ዝንብ አይገባበትም ።

ዝም ፡ አይነቅዝም ።

ዝም ያለ ተንኮለኛ ይመስላል ፡ እንብላ ያለ ስስታም ይመስላል ።

ዝምታ ለበግም አልበጃት ፡ አስራ ሁለት ሆና አንድ ነብር ፈጃት ።

ዝምታ ወርቅ ነው ፤ መናገር ብር ነው ።

ዝቅ ቢል ከገብርዬ ፡ ከፍ ቢል ከዚያ ሰውዬ ።

ዝባድን ከውሻ ፡ እምነትን ከባለጌ አትሻ ።

ዝናር የሌለው ነፍጠኛ ፡ አለንጋ የሌለው ፈረሰኛ ።

ዝናብ ለዘር ጠል ለመከር ።

ዝናብ ሲጥል ሲል ይነፍሳል ።

ዝናብ ሲያባራ ከዋሻ ፤ ምን ሊሻ ።

ዝናብ ሳይመጣ ገና ፤ የውሃ መንገድ መጥረግ ደህና ።

ዝናብ ባይመጣ ሁሉ ቤት ፤ እንግዳ ባይመጣ ሁሉ ሴት ።

ዝናብ ከደመና ፤ ነገር ከዋና

ዝናብ ዘነበ ቢለው ፤ ከደጅህ እየው ።

ዝናብና ልጅ ሲጠሉት ያከብር ።

ዝንብ ሩቅ አይበር ፤ የሚዳ ልጅ ዱር አይደፍር ።

ዝንብ ሳይቅሙ ፤ ዝግን አይቅሙ ።

ዝንብ ቢሰበሰብ መግላሊት አይከፍት ።

ዝንብ ቢሰበሰብ ጋን አይከፍትም ።

ዝንብ ካይን ፤ ጭራ ከዘባን ።

ዝንጀሮ መቀመጫዬ ይብሳል አለች ።

ዝንጀሮ ፤ ሰው ነበር ይላሉ ዱሮ ።

ዝንጀሮ ቢሰበሰብ ውሻን አይመክትም ።

ዝንጀሮ እንሳሳቅ ካልሽ ፤ ነዶዬን መልሽ ።

ዝንጀሮ የቂጧን መላጣ ሳታይ ፤ በባልንጀራዋ ትስቃለች ።

ዝንጀሮና ጥዋ ከፉ ነው የሚይዝ ።

ዝንጀሮን በበግ ለውጠኝ ቢለው ፤ ጣፋጩን ትቼ አልማጩን ።

ዝንጅብል ማን? ቢሉህ ማነኝ ትል ።

ዞር አሉ አልሸሹም ።

ዞሮ ዞሮ ፣ መዝጊያው ጭራሮ ።

ዞሮ ዞሮ ፣ የዶሮ አንገት በማሰሮ ።

## - የ -

የሀምሌ ብራ ፣ የባልቴት ወበራ ።

የሀምሌን ወሃ ጥም ፣ የሀዳርን ራብ የሚያውቅ ያውቀዋል ።

የሃር ገመድ ፣ የበቅሎ ክበድ ።

የሀብታም ልጅ ሲጫወት ፣ የድሃ ልጅ ይሞታል ።

የሀጢአት ክፉ ጉቦ ፣ የበሽታ ክፉ ተስቦ ።

የሀጥኡ ዳፋ ፣ ፃድቁን ያዳፋ ።

የሁለት ሴቶች ባል ፣ ይሞታል ይበላል ሲባል ።

የሁለት አገር ሰደተኛ ።

የሁለት እዳ ከፋይ ።

የሀልም ሩጫ ፣ የጨለማ ፍጥጫ ።

የሆነ አይመለስ ፣ እሳት አይጎረስ ።

የሆድ ማበድ ፣ ያስቃል በግድ ።

የሆድ ምቀኛ አፍ ነው ።

የሆድ ብልሃት ፣ የጋን መብራት ።

የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል ።

የሁዋላ ሁዋላ ፣ አይቀርም ዱላ ።

የለመነ ፣ መነመነ

የለመነ ያገኛል ፣ የነገደ ያተርፋል ።

የለመኑትን የማይነሳ ፣ የነገሩትን የማይረሳ ።

የለመደ ልማድ ፣ ያሰርቃል ከማእድ ።

የለመደ እጅ ፣ ጆሮ ግንድ ያስመታል ።

የለመደ ፈረሰኛ ዛብ አይጨብጥ ፣ እርካብ አይረግጥ ።

የለመደች ጦጣ ፣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ ።

የለማኝ ስልቻ ሲንከባለል ፣ ከለማኝ ደጅ ይወድቃል ።

የለም ቀሪ ፣ ካለ ፈጣሪ ።

የለበሰ ፣ የማንንም ጎረሰ ።

የለበሱት ያልቃል ፣ የሰጡት ያፀድቃል ።

የሊጋስ ምስክሩ መስጠቱ ።

የላሜ ልጅ ፣ ያውራዬ ውላጅ ።

የላም መንጃ ፣ የሸማ መከንጃ ፣ የማር መቅጃ ።

የላም ወተቱን ፣ የጌታ ከብቱን ።

የላከ እንደ አፉ ፣ ያከከ እንደ እጁ ፣ አይሆንለትም ።

የላይ ለምጡን ፣ የውስጥ እብጡን ፣ ባለቤቱ ያውቀዋል ።

የላይ አልጋ ፣ የውስጥ ቀጋ ።

የላይኛው ከንፈር ለክርክር ፣ የታችኛው ከንፈር ለምስክር ።

የላጭን ልጅ ቅማል በላው ፤ ያናጢን ልጅ ጅብ በላው ።

የሌለው ልብ የለው ፣ ወዳጅ የለው ።

የሌለው ሚስት የለው ፣ ወዳጅ የለው ።

የሌሊት ግስገሳ ፣ የቀን ዘለሳ ።

የሌላት እራት ፣ ደግሞ ምሳ አማራት

የሌባ ምኝታው ካመድ ፤ መታሰሪያው ገመድ ።

የሌባ ሞኙ ፤ ከጎተራ ስር ይገኝ ።

የሌባ አይነ ደረቅ ፤ መልሶ ልብ ያድርቅ ።

የሌባ እጁን ፤ የፍየል ልጁን ።

የሌባን ጠባቃ ፤ አደባልቀህ ውቃ ።

የልመና በሬ ትክክል አይሄድም ።

የልመና እንጀራ ምንጊዜም ከልመና አያወጣም ።

የልቡን ሲነግሩት የኮረኮሩትን ያህል ይስቃል ።

የልብ ሳይደርስ ፤ እድሜ ይደርስ ።

የልብህን ቢያናግሩህ ፤ እለ እዳ ቢለቁህ ።

የልብስ ቀላል ፤ ባለቤቱን ያቀላል ።

የልጅ ልጅ እህል ፈጅ ፤ ሁዋላም ጅብ ያስፈጅ ።

የልጅ ልጅ ፤ ጅብ አስፈጅ ።

የልጅ ሞት ፤ የእግር እሳት ።

የልጅ ቀላቢ ፤ የአህያ ጋላቢ ።

የልጅ ብልጥ ፤ እየቀደመ ይውጥ ።

የልጅ ተሚጋች ፤ በፊት ሰማይ ያያል ፤ ሁዋላ መሬት ።

የልጅ ተሚጋች ጢት ሰማይ ሰማይ ፤ ማታ ምድር ምድር ያይ ።

የልጅ ነገር ሁለት ፍሬ ፤ አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ ፤ ።

የልጅ ነገር ፤ ጥሬ በገል ።

የልጅ ከፉ ዲቃላ ፤ የቤት ከፉ ሰቃላ ፤ የልብስ ከፉ ነጠላ ።

የልጅ ከፋቱ ፤ አለመከማቸቱ ።

የልጅ ጥፉ ፣ በስም ይደግፉ ።

የልጅ ፍቅር ፣ የሴት ከንፈር ፣ እናትን ኦያስቀብር ።

የልጅቷን ስጋ በእናቷ ቅቤ ።

የሎሌ አልቃሽ ፣ የሴት ቀዳሽ ።

የመልኳን ሲኳት የጠባይዋን ።

የመሬት ሴሰኛ ፣ ከመንገድ ዳር ይተኛ ።

የመሬት እርጥብ እሾቱን ፣ ደረቅ ምርቱን ።

የመስከረም ውስጡ በጋ ፣ ያረመኔ ልቡ ቀጋ ።

የመቀናጆ በሬ ሲመሽ ወደ ቤቱ ይስባል ።

የመበደሪያ አፍ መከፈያ አይሆንም ።

የመታሰር ምልክቱ መያዝ ፣ የመሻር ምልክቱ መጋዝ ።

የመታሰር ምልክቱ መጋዝ ፣ የመዳኘት ምልክቱ መያዝ ።

የመነነ ከዱር ፣ የሞተ ከመቃብር አይወጣም ።

የመነኩሴ ሎሌ ፣ የክረምት አሞሌ ።

የመነኩሴ ፈራጅ ።

የመንማና ፣ የለው ገናና ።

የመንታ እናት ፣ ተንጋላ ትሞት ።

የመንገድ ዳር እሾት ፣ ባል የሌላት ሴት ለማንም ናት ።

የመከሩበት ሞተ ፣ የወረወሩበት ተሳተ ።

የመከራ ልጅ ሁል ጊዜ መከራ መስሎ ይታያል ።

የመከራ ሎሌ መከራ መስሎ ይታያል ።

የመከራ ውዝፍ ያለበት ነጋዴ ከሚወረር አገር ይደርሳል ።

የመከራን ጉድጓድ ፡ ሚዳቋ አትዘለውም ።

የመኮንን ልጅ በከተማ ፡ የድሃ ልጅ በውድማ ።

የመኮንን ልጅ አዘን ቢነግሩት አደን ።

የመዝሙር መጀመሪያ ሃሌታ ፡ የዘፈን መጀመሪያ እስክስታ ።

የመጠጡት ቅልጥም ፡ ከብርንዶ ይጥም ።

የመጣ ቢመጣ ፡ ከቤቴም አልወጣ ።

የመጥረቢያ ልጅ መዘለፊያ ።

የሙሽራ እድሜ ቢያጥር ፡ የስርጉ ድግስ ሆነ ለተዝካር ።

የሙት ቀናተኛ ፡ ሚስቱን አደራ ይላል ።

የሙት አልቃሹ ፡ የቁም ወራሹ ።

የሙት ፡ የለውም መብት ።

የሚሆን ቢሆን ፡ ዝሆን ይበላ ቢሆን ።

የሚሉሽን በሰማሽ ፡ ገበያም ባልወጣሽ ።

የሚመከተው ጋሻ ፡ የሚጠጋበት ዋሻ የለውም ።

የሚመጣውን እንድታውቅ ፡ ያለፈውን እወቅ ።

የሚሮጡበት ሜዳ ፡ የሚወጡበት ቀዳዳ ።

የሚሰርቀውን ያጣ ሌባ ፡ ሰላማዊ መስሎ ይገባል ።

የሚሰርቅ ሰው አደራ ቢያስቀምጡት እጅ ይነሳል ።

የሚስት መናኝ ፡ የእናት አገር ለማኝ ።

የሚስት አምባሻ ፡ የጎረቤት ውሻ ፡ የደጅ እርሻ ።

የሚስት ወይዘሮ ፡ እርሻው ጋራ ዞሮ ።

የሚሸሹበት አምባ ፡ ሲሸሽ ተገኘ ።

የሚበላው ካጣ ፣ ይበላበት ያጣ ፤

የሚበጀውን ባለቤት ያውቃል ።

የሚከርምም የማይከርምም አንድነት ዝናም ይለምናል ።

የሚካኤል ስለት ለገብርኤል ምኑ ነው ።

የሚወዱትን አቅፎ ፣ የሚጠሉትን ነቅፎ ።

የሚውል ሆድ ማለዳ ይርበዋል ።

የሚዛንን አባይ ለእሳት ፣ የዳኛን አባይ ለሰንሰለት ።

የሚያልቅ እህል ከማያልቅ ዘመድ ያጣላል ።

የሚያልፍ ቀን ፣ የማያልፈውን ስም ያወርሳል ።

የሚያልፍ ነገር ፣ የማያልፍ ስም ይሰጣል ።

የሚያልፍ ውሃ ፣ አደረገኝ ድሃ አለች ልጅዋን ጎርፍ የወሰደባት ።

የሚያልፍ ዝናም አይምታህ ፣ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ ።

የሚያልፍ ዝናም አይምታህ ፣ የሚያድግ ልጅ አይጥላህ ።

የሚያማ ጠበኛ ፣ ዘወር ይበል ከኛ ።

የሚያስፈራውን ለሚነግርህ ፣ የሚያስ ቀዝነውን ንገረው ።

የሚያድግ ልጅ ፣ በእናቱ እጅ ።

የሚያድግ ልጅ አትበድል ፣ የሚሞት ሽማግሌን አታቃልል ።

የሚያድግ ልጅ አይጥላህ ፣ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ

የሚያድግ ዛፍ በቁጥቋጦው ያስታውቃል ።

የሚያጠግብ ቂጣ ከምጣዱ ፣ የሚወጣ ጥጃ ከገመዱ ።

የሚያፈስ ቤት ፣ ጨቅጫቃ ሚስት ።

የሚዳቋ ብዛት ፣ ለውሻ ሰርግ ነው ።

የሚዳቋ ግርግርታ ፥ ለውሻ ሰርግ ነው ።

የሚጣፍጥ ምግብ ምንድ ነው ? ቢሉት ሲርብ የበሉት ።

የሚፈልግ ያገኛል ፥ የሚተኛ ያልማል ።

የሚፈርስ ከተማ ፥ ነጋሪት ቢመታ አይሰማ ።

የሚፈታ ከተማ ፥ አዋጅ ቢነግሩበት አይሰማ ።

የማህበር አሽከር በልቶም አይጠገን ፥ ታሞም አይድን ።

የማሽላ ዘር ፥ ከነአገዳው ቸር ።

የማታ ማታ ፥ እውነት ይረታ ።

የማታ ማታ ፥ ጭምት ይረታ ።

የማታ ምግብ ለእንግዳ ፥ የጧት ምግብ ለአገዳ ፥ የጧት መጠጥ ለእዳ ።

የማታ ሩጫ እንቅፋት ትርፉ ።

የማታድግ ውርንጫ እናትዋን ትመራለች ።

የማታድግ ጥጃ እናቷን ትመራለች ።

የማትሄድ መበለት ፥ ዞራ ዞራ ትሰናበት ።

የማትረባ ፍየል አምስት ትወልዳለች ፥ ልጆቿም ያልቃሉ እሷም ትሞታለች ፥

የማትሰማው ስድብ ከቀረርቶ ይቆጠራል ።

የማነው እህል ? ያሰኘሃል ክምር ፥ የማነው ቤት ? ያሰኘሃል አጥር ።

የማን እርሻ ብለህ እረስ ፥ የማን ሚስት ብለህ ውረስ ።

የማን ገበሬ ሹርባ ይሰራል ።

የማያመሽ ባል ፥ ቅንድብ ይስማል ።

የማያምኑበት ተዘግቶ ፥ ይተውታል ተከፍቶ ።

የማያስተኛ ነግረውህ ፥ ተኝተው ያድራሉ ።

የማያበላ ቢገላምጥ ፣ አያስደነግጥ ።

የማያበድር ደመኛ ፣ የማይመልስ ቀማኛ ።

የማያበድር ገዳይ ፣ የማይመልስ አባይ ።

የማያዋጣ ባል ፣ ቅንድብ ይስማል ።

የማያውቁት አገር አይናፍቅም ።

የማያውቅ ፣ ምን ያውቅ ።

የማያድግ ልጅ ባራስ ቤቱ ዳንኪራ ይመታል ።

የማይገዙ በከፈር ፣ ያግዛሉ በከንፈር ።

የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል ።

የማያፍር እንግዳ ባለቤቱን ይጋብዛል ።

የማይሆን ነገር የተገላቢጦሽ ፣ ያችን ላንቺ ማናለሽ ።

የማይመለስ ማር ፣ ሹመኛ ይበደረዋል ።

የማይመስል ነገር ፣ ለሚስትህ አትንገር ።

የማይመቱት ልጅ ፣ ቢቆጡት ያለቅሳል ።

የማይሰማ ሰው ፣ ልቤን አፈረሰው ።

የማይሰራ አይብላ ፣ የማይረዳ አይጥላ ።

የማይስማሙ ዝንቦች ጥምብ ይልሳሉ ፣ የሚስማሙ ንቦች ማር ይጎርሳሉ ።

የማይቀና ባይወልድ ፣ የማያስብ ባይነግድ ይሻላል ።

የማይበሉት እህል ፣ ከአፈር እኩል ነው ።

የማይበላ የለም ፣ የማይጠግብ ባሰ ።

የማይተማመኑ ባልንጀሮች ፣ በየወንዙ ይማማላሉ ።

የማይተች አይፍረድ ፣ የማያተርፍ አይነግድ ።

የማይቻል ጠላት ፣ ከወዳጅ ይቆጠራል ።

የማይችሉት ድንጋይ ሲያወጡት ደረት ፣ ሲያወርዱት ጉልበት ይመታል ።

የማይከፍል ባለ እዳ ፣ የሰጡትን ይቀበላል ።

የማይዘልቅ ማህበር ፣ በጠጅ ይጀመራል ።

የማያዘልቅ ፀሎት ለቅስፈት ።

የማይደርሱበትን አያኩም ።

የማይድን በሽተኛ በጥር እሸት አምጡ ይላል ።

የማይድን በሽተኛ የበጋ እሸት አምጡልኝ ይላል ።

የማይድን በሽተኛ ፣ የማይመለስ ሃጢአተኛ ።

የማይድን ባህታዊ ወተት አምጡ ፣ የማይድን ቆቅራ ጠላ ስጡ ።

የማይገባ ሱሪ ፣ የማይበቅል ዘሪ ።

የማይጠረጥር ፣ ቤቱን አያጥር ።

የማይጣሉ መላእክት ፣ የማይታረቁ አጋንንት ።

የማይፅፍ ደብተራ ፣ ክንፍ የሌለው አሞራ ።

የማይፈወስ ደዌ ይ ፣ የማይመለስ ጊጉይ ።

የሜዳ ንስንሱን ፣ የቤት ጉስጉሱን ።

የምመከተው ጋሻ ፣ የምጠጋበት ዋሻ ።

የምሮጥበት ሜዳ ፣ የምወጣበት ቀዳዳ የለም ።

የምስራች በቃሏ መላች ።

የምታሽንፈውን ምታ ቢሉት ፣ ወደ ሚስቱ ሮጠ ።

የምትመከተው ጋሻ ፣ የምትሰወርበት ዋሻ ።

የምትሮጥበት ሜዳ ፣ የምትገባበት ቀዳዳ ።

የምትበላው እህል ፣ ከማታየው መሬት ይበቅላል ።

የምትታጠቀው የሌላት ፣ የምትከናነበው አማራት ።

የምትነቃነቅ ግንድና የምትስቅ ሴት ልብ ሩቅ ነው ።

የምትኮነን ነፍስ ጎረቤት ያውቃታል ።

የምትጠላው ሰው ፈሱ እሆዱ ውስጥ ሳለ ይሸታል ።

የምትጠላውን የምትወደውን ሰጥተህ ሸኘው ።

የምትጠባ ጥጃ አትጮህም ።

የምድሩን በአፍ ፣ የሰማዩን በመጣፍ ።

የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ ።

የምጥ መድሀኒቱ አንድ እግር ማስቀደም ነው ።

የሞተ ልጅ አንገቱ ረጅም ነው ።

የሞተ ቢሞት ፣ ያለን እንጫወት ።

የሞተ አይከሰስ ፣ የፈሰሰ አይታፈስ ።

የሞተ ያልነበረ ይመስላል ፤ ያለ የማይሞት ይመስላል ።

የሞተን አትርሳ ፣ የወደቀን አንሳ ።

የሞተው ወንድምሽ ፣ የገደለው ባልሽ ፤ አዘንሽ ቅጥ አጣ ፣ ከቤትሽም አልወጣ ።

የሞተውን አያ ይለዋል ።

የሞት በደለኛ ፣ አይያዝ በዳኛ ።

የሞኝ ልቅሶ ፣ መልሶ መልሶ ።

የሞኝ ሚስት ፣ በምልክት ።

የሞኝ ምስጋና ፣ የማንቦት ደመና ።

የሞኝ በትር ፣ ሆድ ይቀትር ።

የሞኝ እጁን ሁለት ጊዜ እባብ ነከሰው ፤ አንድ ጊዜ ሳያይ ፥ ሁለተኛው ሲያሳይ ።

የሞኝ ዘመድ ያፍራል ።

የሞኝ ጠላ ፥ በለው ባንከላ ።

የሞኝን ጥርስ ብርድ ፈጀው ።

የረዘመን በጠፍር ፥ ያጠረውን በድግር ።

የረዘመውን በጦር ፥ ያጠረውን በድግር ።

የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል ፤ የረጋ ሰው ማለፊያ ይሆናል ።

የሩቁን የሚመለከት ፥ የፊቱን ያፈሳል ።

የራሱን እንዳይበላ ገንዘብ የለው ፥ የሰው እንዳይበላ አመል የለው ።

የራሱን ጥሎ ፥ የሰው አንጠልጥሎ ።

የራስ ጌጥ ስለጨርቅ ፥ የሌላው ያስጨንቅ ።

የራስዋ ቢያርባት ፥ የሰው ታማስላለች ።

የራስዋ ጊዜ አለቀሰች ፤ የሰው ጊዜ ሳቀች ።

የራበው ፥ ይጠግብ አይመስለው ።

የራበውን ገበያ አታውጣው ።

የሬሳ ጎረቤት እሳት አያጫጭር ፥ ቢሞቱ አይቀብር ።

የሮጠ አመለጠኝ ፥ የበላ በለጠኝ ።

የሰለጠነ ፥ ሰየጠነ ።

የሰማ ይሰማ ፥ ያልሰማ ይግማማ ።

ሰማዩ ንጉስ እስኪረዳ ፥ የመሬቱ ንጉስ ይጎዳ ።

የሰማዩን ያህል እንጀራ ይሰጥህ ቢለው ፥ የኮከቡን ያህል በላተኛ አለበት አለ ።

የሰራው ቢረሳ ፥ የተሰራው አይረሳ ።

የሰባን አርዶ ፣ የጠራን አውርዶ ።

የሰነፍ መላሰኛ ፣ የበሽተኛ በላተኛ ።

የሰነፍ አበላል ይብረድልኝ ፣ የሰነፍ ምስክር ይማልልኝ ።

የሰከረ ሲተፋ ፣ የገደለ ሲደነፋ ።

የሰከረ አወዳደቁ አያምር ።

የሰከረ ይተፋል ፣ የገደለ ይደነፋል ።

የሰው ሆዱን ፣ የወፍ ወንዱን የሚያውቅ የለም ።

የሰው ልጅ መከራው እንጀራው ያልቅና ፣ ወጡ ይተርፍና ።

የሰው ልጅ በምን ይታፈራል? በወንበር ፤ አይደለም በወንበር ፣ በከንፈር ።

የሰው ልጅ ቢወልድ ሎሌውን ፣ ባለጌ ቢወልድ ጌታውን ።

የሰው ልጅ ከማሳደግ ፣ የውሻ ልጅ ማሳደግ ።

የሰው ልጅ ካለ አገሩ ፣ ጎራዴ ካለ ሰፈሩ ።

የሰው መሰረቱ ፣ አባትና እናቱ ።

የሰው መዋደዱ ፣ መዋለዱ ።

የሰው መዋደጃው ፣ በየምድጃው ።

የሰው ሞኝ ፣ አንድ እንጨት ያስራል ።

የሰው ስጋ ቢጠብሱት ያራል ፣ ቢበሉት ይመራል ።

የሰው ቀላል ለራሱ ይቀላል ፤ የልብስ ቀላል ባለቤቱን ያቀላል ።

የሰው ቀላል ራሱ ይቀላል ፤ የልብስ ቀላል ለባሹን ያቀላል ።

የሰው ቃሪያ እስቲሞት ድረስ አይበስልም ።

የሰው በልቶ ፣ አያድሩም ተኝቶ ።

የሰው ባህርይ ሳይደርሱ ፣ የድንጋይ ስር ሳይምሱ ።

የሰው ቤት ሲቃጠል ቋያ ይመስላል ።

የሰው ብልሃቱ ፤ ለፈጣሪ መንገር ነው መድሃኒቱ ።

የሰው ብድር ፤ አይቀር በምድር ።

የሰው ታናሽ ፤ ይገዛል በማማሽ ።

የሰው ታናሽ ፤ ይጥላል ጭራሽ ።

የሰው ነገር ፤ አለመናገር ።

የሰው አመሉ ዳውላ ሙሉ ፤ መች ያስታውቃል አብረው ታልኖሩ ።

የሰው አባቱ ሽማ ፤ የሽማ አባቱ ጥለቱ ።

የሰው አባት የሚሰድብ አባቱን የጠላ ነው ።

የሰው አባት የሚሰድብ ፤ አባቱን ያሰድብ ።

የሰው አትበይ ምግባር የለሽ ፤ የራስሽን አትበይ ገንዘብ የለሽ ።

የሰው አገሩ ፤ ምግባሩ ።

የሰው አገር ዝናምና የእንጀራ አባት አይምታህ ።

የሰው እንግዳ ፤ ያገር ባዳ ።

የሰው እጅ ፤ የእግዜር ደጅ ።

የሰው ከማየት ፤ የራስን መብላት ።

የሰው ከርፋፋ ሲሰድቡት አይከፋው ።

የሰው ኩራቱ ፤ በናትና ባባቱ ።

የሰው ክብረቱ ፤ ያሰኘዋል አንቱ ።

የሰው ክፉ ዋሾ ፤ የእፅ ክፉ አብሾ ።

የሰው ክፉ ፤ ጠማማ ነው አፉ ።

የሰው ወርቅ ፤ አያደምቅ ።

የሰው ግብሩ ፣ አይለየው እስከ መቃብሩ ።

የሰው ግብር ቢመለከቱ ፣ ድሃ ይሆኗል ባመቱ ።

የሰው ግብር ፣ እስከ መቃብር ።

የሰው ጠላቱ ፣ ይወጣል ከቤቱ ።

የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል ፤ አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል ።

የሰው ፊት አይቆረስ ፣ የሰው ገንዘብ አይወረስ ።

የሰው ፊት የማያፍር በቅሎ አይቀመጥ ።

የሰው ፊት ደግነቱ ፣ አለመፋጀቱ ።

የሰውን ባህያ ፣ የራስን በጉያ ።

የሰውን ነገር ፣ ስንቱን ልናገር ።

የሰይጣን ክፋቱ ፣ ያለ መታየቱ ።

የሰይጣን ገንዘብ የተበደረ ፣ ሳይበላው ተቀበረ ።

የሰይጣንን አመጣጥ የማያወቅ አይጡንኩስ ።

የሰዳጅ ፣ ለወዳጅ ።

የሰጋ ቤቱን ዘጋ ፣ የዘነጋ ተወጋ ።

የሰጠ ቢነሳ ፣ የለበት ወቀሳ ።

የሰጠኸኝ ሸማ ፣ ከደጅህ ተቀማ ።

የሰጠውን አላህ ማን አልችል ይላል ።

የሰጡህን ተቀበል ፣ ያደረጉልህን ቸል አትበል ።

የሰጡህን አትንሳ ፣ ያደረጉልህን አትርሳ ።

የሰጡን ይሰጧል ፣ የገዙን ይነዷል ።

የሰጡን ይሰጧል ፣ ያጠቡን ያስጧል ።

የሳር ክምር ፣ የጭሰኛ ክብር ።

የሳተ ይምክርህ ፣ የዋለ ይንገርህ ።

የሴት ልቧ እንጂ ፣ ሆዷ አይመርጥም ።

የሴት መልኳ ምንድር ነው ? እጅዋን ታጥባ እንኩ ስትል ነው ።

የሴት መጠጥ ደፋር ፣ የወንድ አይን አፋር ።

የሴት ምክር ፣ የሾህ አጥር ።

የሴት ሞቷ ፣ በማጀቷ ።

የሴት ረኀብ ፣ የማቅ ውኀብ ፣ እምብዛም አያስጎመጂም ።

የሴት ረኀብ ፣ የማቅ ውኀብ አያስጎመጂም ።

የሴት ስካር ፣ ያጭር ሰው ኩራት አይታይም ።

የሴት ቀበጥ የበቅሎ መድን ለመሆን ገበያ ትወጣለች ።

የሴት በራ ፣ የበቅሎ ቦራ ።

የሴት በራ ፣ የበቅሎ ደንባራ ።

የሴት ብቻዋን ሂያጅ ፣ የቄስ አርፋጅ ፣ ሁለቱም ነገር ወዳጅ ።

የሴት አመዳም ፣ የአሮጌ ሆዳም ።

የሴት አመዳም ፣ ያህያ ሆዳም ።

የሴት አገሯ ፣ ባሏ ።

የሴት አገሯ ባሏ ፣ ማደሪያዋ አመሏ ።

የሴት አጭር ወይዘሮ ፣ የወንድ አጭር አውራ ዶሮ ።

የሴት እንግዳ ፣ የመርፌ ጎዳ ።

የሴት ከርፋፋ ዕቃውን በእቃ ደጋግፋ ፣ አንዱን ስታነሳ ሁሉም ይደፋ ።

የሴት ክፉ ምላሰኛ ፣ የበሽታ ክፉ መጋኛ ።

የሴት ክፉ አፈኛ ፣ የኀረቤት ክፉ ምቀኛ ።

የሴት ዘበናይ ፣ የፊቷን እንጂ የሁዋላዋን አታይ ።

የሴት ዘንገኛ ፣ የናት ምቀኛ ።

የሴት ዶሮ ኩኩሉ ፣ ለባለጌ ኩሩ ።

የሴት ጉልበቷ ፣ ምላስዋ ።

የሴት ጠጪ ፣ የግመል ፈንጪ ።

የስራት መቋሚያው ፈጠም ፣ የስጋ መቋሚያው ቅልጥም ።

የስሱ ልጅ ስሱ ፣ መደቆሻ ሲልስ ተሰበረ ጥርሱ ።

የስንዴ ንፍሮ ያተር ድብልቅ ፣ ከዚያችው ወጥተው እዚያችው ጥልቅ ።

የስንዴ አራራ ፣ የሴት መራራ ።

የስንዴ አራራ ፣ የቆንጆ መራራ ።

የስድብ አበጥ የለው ።

የስድብ ክፉ አባት ፣ የብትር ክፉ አናት ።

የስጋ ልል ጭቅና ፣ ያመትባል ትልቅ ገና ።

የስጋ መድሃኒት ላም ፣ የነፍስ መድሃኒት ማርያም ።

የስጋ መጨረሻ አጥንት ፣ የነፍስ መጨረሻ ግዝት ።

የስጋ ቁራጭ ፣ የብርሌ ጭላጭ ።

የስጋ ትል ፣ የዘመድ ጥል ።

የስጋዬ ቁራጭ ፣ የአጥንቴ ፍላጭ ።

የሽማ ጥቅል ፣ የወርቅ እንክብል ።

የሸንነ አይን ጉልበትን ይሰብራል ።

የሹም ሰነፍ ፣ አንዱን ሳይጨርስ አንዱን ይወዝፍ ።

የሹም ሰነፍ ፥ ይለፈልፍ ።

የሹም ከርፋፋ ፥ አገር ያጠፋል ፥ ያህያ ጅላፋ መስክ ያጠፋል ።

የሹም ጦሩ ፥ እቅፍ ሙሉ ።

የሹክሹክታ ግቢ ለፍች ያስቸግራል ፥ ገርጋሪ በቅሎ ይደነብራል ።

የሺ ሞት ሰርግ ነው ፥ ያንድ ሞት ጉዳት ነው ።

የሺ ቃል ንቁፍ ፥ የዋና ቃል ፅሁፍ ።

የሺ አካላት መሰብሰቢያው እናት ።

የሺ ገንዘብ ብላ ፥ ከሺ ወንድም አትጣላ ።

የሺ ገንዘብ ተቀበል ፥ የሺ ወንድም አትግደል ።

የሺ ፍልጥ ፥ ማሰሪያው ልጥ ።

የሺን ገንዘቡን ብላ ፥ ወንድሙን አትንካ ።

የሽሮ ፋከራ ፥ ከምጣዱ እስኪወጣ እንጀራ ።

የሽንኩርት ሌባ አታላይነቱ ፥ ልሽተት ማለቱ ።

የሽኮኮ ዳቦ ለመስበኪያ ፥ ቀጭን ሽማ ለማረግረጊያ ።

የሽኮኮ ፀሎት ።

የቀማኛ የለው እጅ ፥ የበቅሎ የለው ልጅ ።

የቀበሮ ባህታዊ ከበግ መሃል ይፀልያል ።

የቀበጡ ለት አይገኝም ሞት ።

የቀበጡ ለት ሞት አይገኝም ።

የቀባጣሪ አፉ ጠማማ ነው ።

የቀና ሲታጣ ፥ ይመለመላል ጎባጣ ።

የቀን ጨዋታ ፥ አይገኝም ማታ ።

የቀደመው ያገሳታል ፡ ደግሞ ደግሞ ያጎርሳታል ።

የቀድሞ አርበኛ ፡ የቅምጥ ይዋጋል ።

የቀኜ ልጅ ጠጪ ።

የቂል ብትር ፡ ሆድ ይቀትር ።

የቂል ፡ ጓደኛው ቂል ።

የቂጣ እንደሁ ይጠፋል ፡ የማርገዝ እንደሁ ይገፋል ።

የቄስ ልጅ ባገባ ፡ በሜሮን ፊትፍቼ እበላ ነበር አለ ።

የቄስ ምንደኛ ፡ የሴት በትረኛ ።

የቄስ ሞገደኛ ፡ የሴት በትረኛ ፡ አያድርስ ከኛ ።

የቄስ ቀማኛ ፡ የዳኛ ምቀኛ ።

የቄስ ቃል ፡ አንድ ይበቃል ።

የቄስ ነጋዴ ፡ ይሆናል ወንበዴ ።

የቄስ ነጋዴ ፡ ይመስላል ወንበዴ ።

የቄስ አባይ ፡ የደበሎ ተባይ ።

የቅማል ስደት ፡ ከራስ ወርዶ አንገት ።

የቅርቡን በደጅ ፡ የሩቁን ባዋጅ ።

የቅርብ አራሽ ፡ በእንቅብ አፋሽ ።

የቅርብ አዝመራ ፡ ለጤና ።

የቅርብ ጠበል ፡ የልጥ መንከሪያ ይሆናል ።

የቆለኛ ምስክር ከጥይት ይፈጥናል ።

የቆመ ሌባ ፡ የተቀመጠውን ይቀማ ።

የቆመው እግር ቢሆን አሳቢው ራስ ነው ።

የቆረጠ ፤ አመለጠ ።

የቆቅ ለማዳ ፤ የካይላ እንግዳ ፤ ከቤት ሲሉት ወደ ሜዳ ።

የቆቅ አውራ ፤ ይወ ላል ተራራ ።

የቆዳ ጓንታ ለወ ሻ ሰርጉ ነው ።

የቆጡን ስታይ የብብቷን ጣለች ።

የቆጡን አወርድ ብላ ፤ የብብቷን ጣለች ።

የበላ በለጠኝ ፤ የሮጠ አመለጠኝ ።

የበላ ቢሮጥ ፤ አያመልጥ ።

የበላ ቢያብል ፤ ገላው ይናገር ።

የበላ ዳኛ ፤ የወጋ መጋኛ ።

የበላች ብትዘፍን ፤ ያልበላች ታዝን ።

የበላን ሆድ ፤ የወጋን ክንድ ያውቃል ።

የበላው ፤ አብላላው ።

የበላውን ያብላላዋል ፤ የለበሰውን ይበርደዋል ።

የበላይ ፤ አዳባይ ።

የበረታ ከራሱ ፤ የሰነፈ ከዋሱ ።

የበረደውን አሙቆ ፤ የረጠበውን አድርቆ ።

የበሬ ሆዳም ፤ ቢሞት አይጎዳም ።

የበሬ ሻኛማ ፤ የላም ግታማ ።

የበሬ ቀንዱን ፤ የወይራ ግንዱን ።

የበሬ እቃ ፤ እየራሱ አለቃ ።

የበሬ ዳተኛ ፤ በ ሣል ይተኛ ።

የበሬ ዳተኛ ፣ የሴት ምላሰኛ ፣ አታምጣ ወደኛ ።

የበሬ ዶሰኛ ፣ የሴት ምላሰኛ ፣ አያድርስ ወደኛ ።

የበሬም ዋይ ይውላል ገበያ ፣ ስጋው ለመብል ቆዳው ለጠፍር ።

የበሬን ምስጋና አህያ ወሰደችው ።

የበሰለ ይበላል ፣ ጥሬ በምጣድ ይቆላል ።

የበሶ አቅማዳ ተፈቶ ፣ የሌባ አፍ ነጥቶ ።

የበሶ አቅማዳ ተፈቶ ፣ የተሸካሚው አፍ ነጥቶ ፣ ይመስላል ?

የበሽታ ክፉ ቁርጥማት ፣ የሃጢአት ክፉ ቅናት ።

የበሽታ ክፉ እህል ያስወድዳል ።

የበቅሎ እቃ ፣ እየራሱ አለቃ ።

የበደለ ይከሳል ፣ የቀማ ይመልሳል ።

የቡና ስባቱ ፣ መፋጀቱ ።

የቡና ቀዝቃዛ ፣ የሹም ፈዛዛ ።

የባህር ዳር ሲታረስ ፣ ጓጉንቸር ሆድ ይብሳታል ።

የባለስር ፣ ምላሱ አስር ።

የባለቤት ሰነፍ ቤቱን ያዋርዳል ።

የባለቤት አዳይ ጦም ያሳድራል ።

የባለቤት እውር እቃውን ያነሳል ።

የባለጌ ሀይለ ቃል ፣ እንደ ሽመል ይወቃል ።

የባለጌ ሃይማኖት ከጅማት ይከራል ።

የባለጌ ልጅ መብል ያፍር ፣ ነገር ይደፍር ።

የባለጌ ልጅ መንገድ ይፈጅ ፣ ነገር አይፈጅ ።

የባለጌ ልጅ እያደር ይጋሻል ፤ የጨዋ ልጅ እያደር ይበሻል ።

የባለጌ ባለሟል ፣ ቂጥ ገልቦ ያያል ።

የባለጌ ባለሟል ካፍ አታውጡኝ ይላል ።

ባለጌ ተለጣጭ ፣ ከድንጋይ ላይ ተቀማጭ ።

የባለጌ ኩራቱ ፣ እንዲያው በከንቱ ።

የባላባት ልጅ ቤት ሊሰራልህ ነው ያሉት እንደሆን ከስቶ ያድራል ።

የባላገር ስልጡን እሰው ፊት ይቆርሳል ።

የባላገር ስልጡን እጅ ይዞ ያጫውታል ።

የባላገር እንግዳ ሞት ፣ የባልቴት ሳዱላ መሬት ።

የባላገር ዱለት ፣ ይፈታል በኩበት ።

የባል ዘመድ ፣ ባይኑ አመድ ።

የባል ደግነቱ ፣ ባትናገር ሚስቱ ።

የባልቴት ወበራ ፣ የክረምት ብራ ።

የባሰ አለ ሚስትህን አትፍታ ።

የባብ ለማዳ ፣ ያህያ ፍሪዳ የለውም ።

የባብ ልጅ በቅንብቻ ።

የባብ ልጅ በቅንብቻ ፣ ስንቅ በስልቻ ።

የባብና የቤት ፍለጋ ፣ ማነው የሚያወጋ ።

የባእድ ሞኝ ከዘመድህ እኩል አርገኝ ፣ የዘመድ ሞኝ ከልጅህ እኩል አርገኝ ።

የባእድ ፍቅር ፣ የውሃ ጌጥ አንድ ነው ።

የባዳ ሞኝ ፣ ከልጅህ እኩል አድርገኝ ይላል ።

የቤቱ መቃጠል ለትሁዋኑ በጀኝ ።

የቤት ቀጋ ፣ የሜዳ አልጋ ።

የቤት ቀጋ ፣ የውጭ አልጋ ።

የቤት ቀጋ ፣ የዱር አልጋ ።

የቤት ቤት አለው ማጀት ፣ የሆድ ሆድ አለው አንጀት ።

የቤት አመል ገበያ ይወጣል ።

የቤት ጥጋብ አለስንቅ ያዘምታል ።

የብልጥ አይን ፣ ቶሎ ያለቅሳል ።

የብረት ቆሎ ፣ የደንጋይ ንፍሮ ።

የብትር ትህትና ያስመታል ፤ የነገር ትህትና ያስረታል ።

የብዙ ሀዋሳት ፣ መሰብሰቢያው አናት ።

የብድር ሽሮ ፣ ምን ሲል ተጀምሮ ።

የጧልተኛ ሎሌ ሳይሰለፍ ያረጃል ።

የተለፋን ቆዳ ላልተለፋ ፣ መለወጥ ለዘጥ ዘጥ ።

የተላከ ፣ አፋን ለከከ ።

የተላጠ እንጨት ዳግም አይላጥም ፣ ሰው አለ አንድ ጊዜ አይበለጥም ።

የተልባ ስፍር የሀልም እንጀራ ።

የተመረረ ድሃ ፣ ይገባል ከውሃ ።

የተመረጠ እንጨት ለታቦት ፣ የተመረጠ ሰው ለሹመት ።

የተመሰከረ ይፈረዳል ፣ የሰባ ይታረዳል ።

የተመታ ዳኒ ፤ ደም የተፈናጠቀበት ሞተ ።

የተመቸው ገንፎ ያላምጣል ።

የተመኘነውን አገኘነው ።

የተማማሉት ማለኛ ፤ የተጋደሉት ጠበኛ ።

የተማረ መልካም ፤ ጥቃት አያስነካም ።

የተማረ ፤ ነፍሱን የመረመረ ።

የተማረ ፤ ክብሩን መረመረ ።

የተማረ ፤ የተሟረ ።

የተማሪ ጋፍ ፤ መልክ ያጋፍፍ ።

የተማከሩት ዳኛ ያግዛል ፤ የመተሩበት እጅ ይወዛል ።

የተሟጋች ፤ ሚስቱ ቧጋች ።

የተረገዘ በሆድ ፤ የታዘለ በለምድ ።

የተራበ አይዘፍንም ፤ የጠገበ አያርፍም ።

የተራበ ከባቄላ ፤ የተበደለ ከሰቀላ ።

የተሳለ ብረት ፤ አንገትን ከደረት ፤ ስጋን ከጅማት ይለያያል ።

የተሸሸገ ምግብ ሆድ አይጠፋለትም ።

የተሸሸገ ምግብ ፤ የተሸሸገ ሆድ አያጣም ።

የተሸከመው ክብዶታል ፤ እንደገና ይጨምርበታል ።

የተሾመ ወደ ግምጃ ፤ የተሻረ ወደ ሙጃ ።

የተሾመን ይሟገቱበታል ፤ የተሻረን ይመሳከሩበታል ።

የተቀመጠ ማርና ልጃገረድ የሚሆኑት አያጡም ።

የተቀማጭ ፤ ምላሱ ምላጭ ።

የተቀማጭ ፤ አፉ ምላጭ ።

የተቆለፈ ወርቅ ፤ ያልተቆለፈ ጨርቅ ።

የተበደለ ከነጋሽ ፤ የተጠማ ከፈሳሽ ።

የተታታ ገመዴ ፣ የተቆፈረ ጉድጓዴ ።

የተነቃነቀ ጥርስ ሳይወልቅ አያርፍም ።

የተናቀ መንደር ባህያ ይወረራል ።

የተናገሩት ከሚጠፋ ፣ የወለዱት ይጥፋ ።

የተኛን አንበሳ ፣ አስነሳችው ላም ልሳ ።

የተኛቸው ሳለች ፣ ያዳመጠችው አረገዘች ።

የተከፋ ፣ ተደፋ ።

የተከፋ ፣ ጨርሶ ተደፋ ።

የተወለዱት ይራባሉ ፣ እንደገና ይወልዳሉ ።

የተዘጋ ተጠበቀ ፣ ያልተዘጋ ተሰረቀ ።

የተደረገ ተደርጎ ፣ እንዳለ መስማት በጎ የለም ።

የተደፋ ሬሳ ፣ የተጠበሰ አሳ ።

የተገኘ ጥበብ ፣ ከዶሮና ከንብ ።

የተገዘተች ነፍስ ፣ የተለጎመች ፈረስ ።

የተጠማ ከፈሳሽ ፣ የተጠቃ ከነጋሽ ።

የተጠረጠሩበት ፣ ድንጋይ ይጥሉበት ።

የተጠገነ እጅ እንደቀድሞው አይሆንም ።

የተጣደፈን ቅቤ ይንቀዋል ።

የተፃፈ ይወረሳል ፣ በቃል ያለ ይረሳል ።

የተፈተለ ይለበሳል ፣ የተጀመረ ይጨረሳል ።

የተፈጠመ አይናገር ፣ እንካሳ አይሻገር ።

የተፈጠመ ያርፋል ፣ የተኛ ያኮርፋል ።

የተቆተን ነገር መልሰው ቢውጡት ፣ ተራራ ያህላል ።

የታለህ ያላሉት ፣ እዚህ አለሁ ይላል ።

የታመመውን ሙት ጠየቀው ።

የታመነ ሎሌ ፣ ጠጅ የመላበት ብርሌ ።

የታቀፈችው እናቲቱ ፣ የሚላጨው አባቱ ።

የታነቀ የልቡን ይናገራል ፣ ግን የሚያምነው የለም ።

የታናሽ ልጅ አሳናሽ ፣ የዘንጋዳ ወጥ እህል አበላሽ ።

የታደለ ፣ ተደላደለ ።

የታደለች ሴት ፣ በፊት ትወልዳለች ሴት ።

የታደለች ቤት አሮጌ ታያለች ።

የት ላይ ተቀምጠሽ ፣ እግዜርን ታሚያለሽ ።

የት ትሄዳለህ? እሁዳዳቸው ፤ ምን ያሮጥሃል? ውቃቢያቸው ።

የት አውቅሽ ብሎ ፣ አጥብቆ ሳመኝ ።

የትም ተከሰስ ፣ አለቃህ ድረስ ።

የትም ተወለድ ፣ አንኮበር እደግ ።

የትም ፍጪው ፣ ዱቄቱን አምጪው ።

የትምህርት ሙግት ፣ አንድ ተናግሮ ጉልት ።

የትንሽ ሰው ፍቅር ፣ በመቀምቀሚያው ጥቁር ።

የትእቢት ፣ መድሃኒቱ ጭንቀት ።

የትውልድ ጉልበቱ ፣ ህብረቱ ፤ የህዝብ ሀብቱ ፣ አንድነቱ ።

የቸኮለ አፍሶ ለቀመ ።

የቸገረው እርጉዝ ያገባል ።

የቸገረው ዱቄት ከነፋስ ይጠጋል ።

የችግር ከፉ እህል ማጣት ፤ የሃጢአት ከፉ ነፍስ ማጥፋት ።

የነሃሴ ውሃ ጥሩ ነው፤የሚጠጣው የለም ፤ የድሀ ነገር ፍሬ ነው፤የሚሰማው የለም ።

የነ ቂሉ ቤት ፤ ግድግዳው ሰንበሌጥ ።

የነበረ ይናገር ፤ ያየ ይመስክር ።

የነበረ ፤ ገብርኤል ተወገረ ።

የነብር ልጅ አይታቀፍ ፤ የጨዋ ልጅ አይነቀፍ ።

የነብር አይን ከፍየል ፤ የፍየል አይን ከቅጠል ።

የነብርን ጅራት አይዙም ፤ ከያዙም አይለቁም ።

የነብርን ጅራት አይጨብጡም ፤ ከጨበጡም አይለቁም ።

የነ ቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ ።

የነገሩ ሁነኛ ፤ የጠሩ አርበኛ ።

የነገሩትን የማይረሳ ፤ የለመኑትን የማይነሳ ፤ እግዜርን አትርሳ ።

የነገር ትህትና ያስረታል ፤ የብትር ትህትና ያስመታል ።

የነገር ወጡ ፤ ማዳመጡ ።

የነገር ጠማማ በሽማግሌ ይታረቃል ።

የነገር ጣእሙ ዝግታ ፤ ያዋቂ ጣእሙ ዝምታ ።

የነገደ አተረፈ ፤ ያለፈ ተራገፈ ።

የነጋሪት በቅሎ ፤ ከላይሽ ማን ወርዶ ።

የነፍሰ ገዳይ ምልክቱ ፤ ደም በጣቱ ።

የነፍስ ትቶ የገብስ ።

የኑሮ ከፉ ደባል ፤ የመንገድ ከፉ ገደል ።

የኑግ ገለባ ፡ እያገርሀ ግባ ።

የናት ሆድ ዠንጉርጉር ነው ።

የናት ሆድ ዠንጉርጉር ፡ ወላጅ ቀይና ጥቁር ።

የናት ልመና ፊት አያስመልስ ፡ አንገት አያስቀልስ ፤ ሲሆን በውድ ፡ አለዚያ በግድ ።

የናት ልጅ ቢጣላ እውነት ይመስላል ።

የናት ልጅ የሌለው አይበላ ፡ ጆሮ የሌለው ምንቸት አይፈላ ።

የናት ልጅ ፡ የጎን እጅ ።

የናት ሞትና የእግር እሳት እያደር ያንገበግባል ።

የናት ሞትና የደንጋይ መቀመጫ እያደር ይቆረቁራል ።

የናትን ክፋት ፡ የደመናን ውሃ ጥማት ፡ ባለቤት ያውቃል ።

የኔ ነህ በለኝ ፡ ደስ እንዲለኝ ።

የኔን ችግር ፡ ለማን ልንገር ።

የኔን ወጥ በቀመስሽው ፡ ያንቺን በደፋሽው ።

የንጨት ምንቸት ራሱ አይድን ፡ ሰው አያድን ።

የንጨት ወልጋዳ ፡ የመንገድ አንጋዳ ።

የንጨት ክፉ አባሎ ፡ የዳኛ ክፉ መድሎ ።

የንፉግ ለጋስ ፡ የሰጠውን ይወርስ ።

የንፉግ ገንዘብ በለጋስ እጅ ይገኛል ፤ የጠላት ገንዘብ በወዳጅ እጅ ይገኛል ።

የንፍጣም ነገሩ አይጥም ።

የአህያ ባል ፡ ከጅብ አያስጥል ።

የአህያ ፍሪዳ ፡ የእባብ ለማዳ የለውም ።

የአልኮል ፍቅር ፡ እስከመቃብር ።

የአመል ታናሽ ፡ ይጥላል ጭራሽ ።

የአምላክ ነገር ፡ አይመረመር ።

የአረፋውን ሲሏት የጀጀባውን ።

የአርበኛ ልጅ ይዋጋል ፡ የአርጌ ልጅ ያወጋል ።

የአስር እናት ፡ ጅብ በላት ።

የአቡነ ዘበሰማያት ጦር ፡ ሲወጋ እንጂ አይታይም ሲወረወር ።

የአተር ክምር ፡ የጢሰኛ ክብር ።

የአንበሳ ልጅ ሲሞት ቅበር ፡ አንበሳ ሲሞት እቤትህ ዋል ።

የአንበሳ ገራም ፡ ይውላል ከላም ።

የአዋጁን በጆሮ ።

የአይን ህመም ክሱት ነው ፤ የሆድ ህመም ልማም ነው ።

የአይን ጨንቋራ ሰው ያየዋል ፡ የልብን ጨንቋራ እግዜር ያየዋል ።

የአይጥ እርጉዟ ፡ የድመት ወዟ ።

የአይጥ ሞትዋ ፡ የድመት ጨዋታዋ ።

የአዳኝ ውሻ መነፅሩ ከአፍንጫው ነው ።

የአገር ጠላት ሽፍታ ፡ የገንዘብ ጠላት መሸታ ።

የአፍ ብልሀት ጌትነት ፡ የእጅ ብልሃት ባርነት ።

የአፍ ዘመድ ፡ ከገበያም አይገድ ።

የእህል ጌታ ፈርዛዛ ፡ የወርቅ ጌታ ቀበዝባዛ ።

የእህል ጣእም በጉሮሮ ፡ የነገር ጣእም በጆሮ ።

የእህት ልጅ ፡ ባይወልዱትም ልጅ ።

የእረኛ ፡ ፈሱ መርዘኛ ።

የእሬትን ምሬት ያልቀመሰ ፥ የማርን ጣእም አያውቅም ።

የእሳት ልጅ አመድ ።

የእቡይ ልጅ ወዳቂ ፥ የዘማ ልጅ ሳቂ ።

የእብድ ቅል ፥ ማንጠልጠያው ክር ።

የእብድ አሞራ ፥ ሲላ ደንገጡሯ ።

የእብድ አጫዋች ሙር ነው ።

የእብድ ዘመድ ሳያማስን አይሰድ ።

የእብድ ገላጋይ ፥ ሾተል አቀባይ ።

የእናት ልጅ ፥ የጎን አሳጅ ።

የእንቢተኛ መድሀኒቱ ዳኛ ።

የእንቧይ ካብ ።

የእንጀራ ቀንጣቢ ፥ የድመት አላቢ ።

የእንጀራ እናት ፥ ምን አጠናሽ እንደ ጅማት ።

የእንግዳ ቅብጢ ፥ ባለቤት ያጎርሳል ።

የእንግዳ ችኩል ፥ ባለቤቱን ያጎርሳል ።

የእንጦጦ መምር ቢናገር ባመት ፥ ያውም ሬት ።

የእከክ መድሀኒቱ ፥ አለመቅረብ አለመቀራረብ ነው ።

የእውር ልቡ ፥ ኢየሩሳሌም ነው አሳቡ ።

የእውር ሞቱ ፥ የጨረቃ ንጋቱ ።

የእውር ቀበጥ ከመሪው ጋር ይጣላል ።

የእውር ነፍጠኛ ፥ የወንበር ፈረሰኛ ።

የእውር አስተናባሪ ፥ የድውይ አጋፋሪ ።

የእውር አዝማሪ ፣ የደንቆሮ ተጣሪ ።

የእውር አፍጣጭ ፣ የንጉስ ቀላዋጭ ።

የእውር ግልምጫ ፣ ያንካሳ ሩጫ ።

የእውነት በትር ትቀጥናለች እንጂ አትሰበርም ።

የእውነት ዘንግ ትመነምናለች እንጂ አትሰበርም ።

የእጅ ብልሃቱ ባርነቱ ፣ የአፍ ብልሃቱ ጌትነቱ ።

የከረረ ይበጠሳል ፣ የበደለ ይወቀሳል ።

የከረረ ይበጠሳል ፣ የተበደለ ይካሳል ።

የከሳ እሪያ ይገራል ።

የከብት አገሩ ባለቤቱ ፣ የሰው አገሩ ምግባሩ ።

የከተማ ዳንዴ ፣ የበረሃ ወንበዴ ።

የከተማን ወሬ መስማት ፣ ትልቅ አዳራሽ መስራት ።

የከፋ እውነት ፣ የተፈጠረ ነው ከውሸት ።

የካህን አፉሩ ፣ ያህያ እውሩ ።

የካህን አፉር ፣ ያህያ እውር ፣ የሴት ደፋር አይረባም ።

የክረምት ጥማትና የመከር ጊዜ ራብ ፣ አለባለቤቱ የሚያውቀው የለም ።

የክፉ ልጅ እናት ሁል ጊዜ ታለቅስ ።

የክፉ ልጅ እናት ሁለት ጊዜ ታዝናለች ።

የክፉ ሰው ተዝካሩ ያቅራል ።

የክፉ ሰው ተዝካር ፣ ውሃ ያስወስዳል በህዳር ።

የኮራ ተጎዳ ፣ አይዋጋም የበሬ ቆዳ ።

የኮሶ ማግስት ፣ እናት በሆነች አራት አምስት ።

የወለደ ይልሳል ፣ የበደለ ይከሳል ።

የወለደውን ሲስሙለት ፣ የደገሰውን ሲበሉለት ደስ ይለዋል ።

የወለደውን ቢስሙለት ፣ ያቀረበውን ቢበሉለት ።

የወለዱት ሁሉ ካደገ ፣ የዘሩት ሁሉ ከፀደቀ ።

የወለፈንድ ስልቻ ፣ ጤፍ ይቋጥራል ፣ ባቄላ ያፈሳል ።

የወለፈንድ ኑሮ ፣ በሁዳዴ ቋንጣ በፋሲካ ሽሮ ።

የወላጅ ሆድ ቀጥቀጥ ፣ የልጅ ሆድ ቀጥ ።

የወረት ኮሶ ይጣፍጣል ።

የወረት ውሻ ፣ ስሟ ወለተ ጴጥሮስ ።

የወረወርኩት እንካሴ ፣ ተመልሶ ለራሴ ።

የወረደ መአቱን ፣ የመጣ ምጣቱን ።

የወሬ ቆርፋዳ ፣ ዋንጫ ቅቤ አያርሰውም ።

የወርካ ልጅ ሳንቃ ፣ ያለቃ ልጅ አለቃ ።

የወሰን ላይ ሰዎች ፣ ሌቦች ወይም ሽፍቶች ።

የወታደር ፈዛዛ ፣ የናት ነዝናዛ የለውም ።

የወንድ ልጅ ሞት ፣ ያደረገውን የዘነጋ ለት ።

የወንድ አልጫ ፣ የእንዶድ ሙቀጫ ።

የወንድ አጭር ዝንጀሮ ፣ የሴት አጭር ወይዘሮ ።

የወንድም ልጅ ባይወልዱትም ልጅ ።

የወንድምህ ጢም ሲላጭ ፣ ጢምህን ውሃ አርስ ።

የወንዶች ባል ፣ አይተህ ማር ።

የወንጭፍ ድንጋይ ባልነበር ፣ የማሽላ እሸት መልካም ነበር አለች ወፍ ።

የወይን ዘለላ ፡ ጋን ይሞላ ፤ የስንዴ ዛላ ፡ እፍኝ ይሞላ ።

የወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛበታል ።

የወደቀን አንሳ ፡ የሞተን አትርሳ ።

የወደደ ሰው አይንም የለው ።

የወደደውን አቅፎ ፡ የጠላውን ነቅፎ ።

የወደዱትን ቢያጡ ፡ የጠሉትን ይቀላውጡ ።

የወደድሽው ቂጣ ፡ ሰተት ብሎ ወጣ ።

የወዳጅ ስልቻው ፡ እየብቻው ።

የወዳጅ ተጋፊ ፡ የጠላት ደጋፊ ።

የወዳጅ ከዳተኛ ፡ አዱኛ ።

የወዳጅና የኮርቻ ፡ አለመንካቱ ብቻ ።

የወጋ መጋኛ ፡ መቅቡጥ የለመደ ዳኛ ።

የወጋ ቢረሳ ፡ የተወጋ አይረሳ ።

የወጣ ሰው አንዱን ጥሎ ፡ አንዱን አንጠልጥሎ ።

የወጣ ቢገባ የገባ ይወጣል ።

የወፍ ወንዱን ፡ የሰው ሆዱን ፡ የሚያውቅ የለም ።

የወፍ ዘላ ፡ ከቤት ይውላል አሽን ሲፈላ ።

የወፍጮ እንጉርጉሮ አይሆንም ለሰርግ ።

የዋህ ፊቱን ቢመልስ ፡ ማጅራቱ ጋራ ይመስለዋል ።

የዋለች ውላ ፡ ባልዋ ሲመጣ ትበላ ።

የዋልንበትን አረም በላው ።

የዋስ ተሚጋች ፡ የቆማጣ ፈትፋች ።

የዋስ ተሟጋች ፣ የድውይ ፈትፋች ።

የዋስ ወንድም አይታገት ፣ የአበያ ወንድም አይጎተት ።

የዋኘ ይሻገራል ፣ የሰራ ይከብራል ።

የዋጋ ብልጥ ፣ ልብ ይግጥ ።

የዋጋ ብልጥ ልብ ይግጥ ፤ የልጅ ብልጥ እየቀደመ ይውጥ ።

የወሃ ሽታ ፣ የባብ ፍለጋ የለውም ።

የወሃ ወሃ ፣ ምን አለኝ ቅሃ ።

የወሃ ጡር በድፍ ያስታጥባል ።

የውስጥ አንጀቴን ፣ የላይ ቁርበቴን ።

የውሻ ትህትና ፣ የካህን እብድና ፣ መቼ ይጋጠምና ።

የውሻን ጥርስ ባጥንት ይፈሯል ።

የውሽማ ሞት ፣ ፊት አይነጭለት ።

የውድማ ዘንዶ ፣ ይቀጠቀጣል እንደ በረዶ ።

የዘላን ቤት ሁልጊዜ ስደት ።

የዘላን ጠመኛ ፣ ከጥጃ ጓዳ አታስገቡኝ ይላል ።

የዘመተ ይመለስ ፣ የገደለ ይንገስ ።

የዘመኑ ሰው ምላሱ መንታ ፣ አንዱ ለፍቅር አንዱ ላሜታ ።

የዘመኑ ሰው ሲያቀርቡት ይርቃል ፣ ሲወዱት ይጠላል ።

የዘመኑ ወሬ ፣ ይቀዳል ባቦሬ ።

የዘመኑ ጫጩት ፣ ከአውራ እኩል ልዋጥ ይላል ።

የዘመድ ለማኝ ፣ ከዝምድናው ወጥቶ ፣ የለመነውንም አጥቶ ።

የዘመድ ሎሌ ፣ የፈረስ ሙሌ ፣ ሲወጣ ወጥቶ ነው ።

የዘመድ ቂስ ፥ እየፈታ ያለቅስ ።

የዘመድ አዳይ ጦም ያሳድራል ።

የዘመድ ዘመድ ወንዝ ያሻግራል ።

የዘመድ ጥል ፥ የስጋ ትል ።

የዘማ ልጅ ሳቂ ፥ ያባያ ልጅ ወዳቂ ።

የዘሬን ብትው ያንዘርዝረኝ ።

የዘነጋ በሩን ዘጋ ።

የዘነጋ ቤቱን ዘጋ ።

የዘነጋ ፥ ተወጋ ።

የዘነገነ አዘነ ፥ ያልዘገነም አዘነ ።

የዘገዩ ፥ ተለዩ ።

የዘፈን መጀመሪያው እስክስታ ነው ።

የዚህ አለም ፍቅር ሰኞ አዲስ ፥ ማክሰኞ ልብስ ፥ ረቡእ ብጥስጥስ ።

የዝሆን ክሳት ፥ የባለፀጋ ድህነት አይታወቅም ።

የዝንብ ሽውታ ፥ የነገር ስልት ይበጥሳል ።

የዝንብ ተላላ ካንድ በሬ ደም ይቀርባታል ።

የዝንብ ተባቱ ፥ የ—ጭምቱ ፥ ሳይታወቁ ሞቱ ።

የዝንጀሪትዩ ዝንጀሪት ፥ ባሌ ገደለ በነጋሪት ።

የዝንጀሮ ልጅ ከዛፍ ፥ የመምህር ልጅ ከመፅሃፍ ።

የዝንጀሮ መነኩሴ ፥ የሰንበሌጥ አንካሴ ።

የዝንጀሮ መንገድ ፥ ከገደል ያደርሳል ።

የዝንጀሮ ንጉስ ፥ እሱው ይከምር እሱው ያፈርስ ።

የዝንጀሮ ጎልማሳ የውሻ ራት ይሆናል ።

የዞረ ምን ያመጣ፣ ፈራና ፈንጣጣ ።

የዞረ ምን ያመጣል? ፈንጣጣ ።

የየጁ ቄስ ቅኔው ቢጎድልበት ፣ ቀረርቶ ሞላበት ።

የያዘውን ከወረወረ ፣ ፈሪ አይባልም ።

የደላው ሙቅ ያኘካል ።

የደላው ውሻ ማር ይቀላውጣል ።

የደመና ውሃ ጥምና የእናት በደል አይታወቅም ።

የደበሎ ተባይ ፣ የዳኛ አባይ ፣ ቢገልጡት አይታይም ።

የደባ ገበያ ፣ በሬው ባስር ፣ ቆዳው በሃያ ።

የደንቆሮ ለቅሶ ፣ መልሶ መልሶ ።

የደንቆሮ ተጣሪ ፣ የእውር አዝማሪ ፣ ዞዋሪ ።

የደንቆሮ ዘፈኑ ፣ ያው አንድ ብቻ ነው ።

የደገመ ፣ ተረገመ ።

የደፋት ሬሳ ፣ የጠበሱት አሳ ።

የዱሮ አርበኛ የቅምጥ ይዋጋል ።

የዳበ ልብ ልቡ ፣ የዳገት ጥግ ጥጉ ።

የዳኛ ልል ያማታል ፣ የአባል ልል ያፋታል ።

የዳኛ ጅሉ ያማታል ፣ ያመል ክፉ ያፋታል ።

የዳኛ ጅል ፣ ያማታል አባይ ምስክር ያስረታል ።

የዳገት ሩጫ ፣ የባለጌ ጡጫ ።

የዳገት በረዶ ፣ የቆላ ዘንዶ ።

የዳጉሳ እንጀራ በትኩሱ ፣ የባእድ ፍቅር በአዲሱ ።

የድሃ ማጀት ቃጢ ማር ለማስቀመጥ አይችልም ።

የድሃ ቁምነገሩ ፣ ገብስ ከናሰሩ ።

የድሃ ብድር ፣ አይውል አያድር ።

የድሃ ተዝካር ፣ የጎባጣ ስካር ።

የድሃ ነገር ማንገቻ የለውም ።

የድሃ ጉልበት በገለባ ያልቃል ።

የድሃ ጉልበት ፣ በገበያ ያልቃል ።

የድሃ ጠላ ፣ ጢት አልፈላ ፣ ማታ አተላ ።

የድመት ማንቀላፋት ፣ አይጦችን ለማጥፋት ።

የድንጋይ ልብ ፣ የኩበት ማምብ ።

የድንጋይ መቀመጥና የባእድ ፍቅር ፣ አያድር ይቀረቀር ።

የድንጋይ ንፍሮ ፣ የብረት ቆሎ ።

የድንጋይን ጠርነት ፣ የሸሮን ቀለብነት ፣ የሚስትን ባርነት ።

የድፍድፍ ኩራት ፣ ውሃ እስኪገባበት ።

የዶሮ አንገት ፣ ከምንቸት ።

የጀመሩትን መጨረስ ፣ የቀረሱትን መጉረስ ።

የጅብ ሁለት ስብሩ ፣ የባለጌ ወታደሩ አስቸጋሪ ነው ።

የጅብ ለማዳ ፣ ያህያ ፍሪዳ የለውም

የጅብ ችኩል ቀንድ ይነከሳል ።

የጅብ ችኩል ቀንድ ይነከሳል ፤ ያይጥ ችኩል የድመትን አፍንጫ ይልሳል ።

የጅብ እንግዳ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል ።

የጅብ ገበሬ ፡ የአህያ በሬ ፡ የጠጣ ዘር አቀባይ ፡ የዝንጀሮ ጎልጓይ ፡ ሁሉም እበላ ባይ ።

የጅብ ጓደኛ ከጥንብ ያደርሳል ።

የጅብ ፈሪ ፡ የሞት ቀሪ ።

የገማ ሰው ሰውን አይሸሽም ፡ ሰው እርሱን ይሸሻል እንጂ ።

የገበያ ሽብር ፡ ለሌባ ሰርጉ ነው ።

የገበያ ሽብር ፡ ለቀጣፊ በጀው ።

የገበያ ወንድና የታሰረ አንበሳ ፡ በብላሽ ያገሳ ።

የገበያ ግርግር ለሌባ ይመቻል ።

የገብስ ብዙ ነዶ ፡ የጤፍ ስሱ ነዶ ።

የገንዘብ እሮጌ ፡ ያባት ባለጌ የለውም ።

የገዛ ጌታ ፡ እግር ይዞ ይመታል ።

የገደለ ባልሽ ፡ የሞተ ወንድምሽ ፤ አዘንሽ ቅጥአጣ ፡ ተቤትሽ አልወጣ ።

የገደል ማሚቶ ፡ ዳቢ ልስጥሽ ድፎ ።

የጉልበት ገሚሱ ምላስ ነው ።

የጉልበት ግማሽ አፍ ነው ።

የጉም ሌባ ፡ ጉሙ ሲጠፋ ወይፈት ትገባ ።

የጉሮሮን መታነቅ ፡ ያይን መደንቆል ያስጥለዋል ።

የጋራ ፡ ወንጋራ ።

የጌታ ሆድ ፡ ጥዋት ከባድ ማታ ወላድ ።

የጌታውን አመካከት ፡ ሎሌው ይመልከት ።

የግመል መጫኛ ፡ ቢበጠስ ላህያ ይበቃል ።

የግፍ ግፍ ፡ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ።

የጎረቤት ሌባ ቢያውቁት ይስቃል ፣ ባያውቁት ያሰጋል ።

የጎረቤት ሌባ ቢያዩት ይስቃል ፣ ባያዩት ይሰርቃል ።

የጎረቤት አሳብ ከገበያ አይወጣም ።

የጎበዝ ልቡ ከደረቱ ፣ የፈሪ ልቡ ከፊቱ ።

የጎበዝ ሹም ፣ የሀዳር ጉም ፣ አገር ይደረግም ።

የጎበዝ ሹም ፣ የጎንደር ጉም ፣ አገር ይደረግም ።

የጎበዝ አሰሳ ፣ የወሬ አፈሳ ፣ ይደርሳል እግር ሳይነሳ ።

የጎበዝ ክምር ፣ እያደር ይጨምር ።

የጎበዝ ዱዳ ፣ ባመቱ ምድረ በዳ ።

የጎበዝ ጉልበቱ ፣ ከደረቱ ።

የጎደለው ሊሞላ ፣ የተረፈው ሊከላ ።

የጎጃም አዝመራ ሽምብራ ነው አሉ ፣ እኛም እንዳንበላ ተነቀለ አሉ ።

የጓጉንቸር ልጅ መሄድ ሳትማር መዝለል ተማረች ።

የጠላ ክፋቱ ፣ አለመገኘቱ ።

የጠላ ክፋቱ አለመገኘቱ ፣ የልጅ ክፋቱ አለመስማቱ ።

የጠመመውን አቅንቶ ፣ የጎደለውን ሞልቶ ።

የጠረጠረ ስንቁን ቋጠረ ።

የጠረጠረ ፣ ቤቱን አጠረ ።

የጠሩት እንግዳ ፣ እራቱ ፍሪዳ ።

የጠበቀ ከራራ ፣ ባጥና ጣራ ።

የጠብ መነሻ ፣ የስብስቱ እርሻ ።

የጠብ መነሾ ፡ አበድሪኝ እርሾ ።

የጠንቀኛ ፈስ ፡ አይን ያፈስ ።

የጠይብ ጂል ፡ ትበላለች በገል ።

የጠጅ ቤት አዛዥ ፡ አተላ አጋዥ ።

የጠጅ ቤት አዛዥ ፡ አተላ አፋሽ ።

የጠገበ ሰው ራሱን አያስብም ።

የጠገበ ሰው ራብን አያስብም ።

የጠገበ ሰው የተራበ ያለ አይመስለውም ።

የጠገበ አበደ ።

የጠገበ እንግዳ ፡ ሳይተኝ አይወጣም ።

የጠገበ እውር ዘንጉን ይወረውራል ።

የጠገበች ዶሮ ከነጭልፊት ማህበር ትገባ ።

የጠጉር ጥቁሩ ፡ የነገር አጭሩ ።

የጢስና የልጅ መውጫው አይታወቅም ።

የጣመው ፡ ቀለጠመው ።

የጣታ በሬ ፡ ለነገ ብሎ ይጠጣል ዛሬ ።

የጣውንት ዶግ ፡ የእንቧጮ ዘንግ የለውም ።

የጥር በልግ ፡ የብር ዘንግ ።

የጥርስን እድፍ ፡ የራስን ጉድፍ

የጥቁር ሴት ንቅሳት የምንድነውን ቢለው ፡ የእግዜር ቁጣ ነው አለው ።

የጥቅምት በረዶ ፡ የጫካ ላይ ዘንዶ ።

የጥቅምት እርሻ ፡ የናት ጉርሻ ።

የጥቅምት እርሻ ፡ ያባት ውርሻ ።

የጥጋብ ለት ሁሉ አንበሳ ፡ የራብ ለት ሁሉ ሬሳ ።

የጠመኛ ፡ ምቀኛ ።

የጠም ቆሎ ፡ የቁልቁለት በቅሎ ።

የጠም ቆሎ ፡ የበአል ዶሮ ።

የጠር ስለቱ ፡ መዋጋቱ ።

የጠርነትን ነገር ፡ ከፈሪ ጋራ አትምከር ።

የጠጣ ልጅ በዛፍ ፡ የመናፍቅ ልጅ በመፃፍ አይቻሉም ።

የጠጣ ብልጣ ብልጥ ፡ የዝንጀሮ ቅልጣ ቅልጥ ።

የጠጣ ዘር አቀባይ ፡ የዝንጀሮ ጎልጓይ ።

የጠጣን ልጅ በዛፍ ፡ የፀጋን ልጅ በመፅሀፍ ማን ይችላል ።

የጧት ለማኝ ለማታ ።

የጧት መጠጥ ለእዳ ፡ የጧት ምግብ ለአገዳ ፡ የማታ ምግብ ለእንግዳ ።

የጨለማ አፍጣጭ ፡ የእውር ገልማጭ ።

የጨለማ ገልማጭ ፡ የእውር አፍጣጭ አይረባም ።

የጨረቃ ሂያጅ ፡ የምስክር ፈራጅ ።

የጨረቃ ንጋትና የእውር ሞት አይታወቅም ።

የጨርቅ ነጩ ፡ የበሬ ልጩ ።

የጨነቀው ይዋጋል ፡ ያልደረሰበት ያወጋል ።

የጨዋ ልጅ ሁሉ ፡ እርግዟል በሆዱ ።

የጨዋ ልጅ ሲያዝን ፡ እሳ በወንዝ ይመከን ።

የጨዋ ልጅ ሲፋታ ፡ ይጋባ ይመስላል ።

የጨዋ ልጅ ከከተማ ፣ የድሀ ልጅ ከውድማ ።

የጨዋ ልጅና ቅል ተሰባሪ ነው ።

የጨው ገደል ሲናድ ሞኝ ይስቃል ፣ ብልህ ያለቅሳል ።

የጨው ገደል ሲናድ ብልህ ያለቅሳል ፣ ሞኝ ይልሳል ።

የጨውን ባለዳ በጨው ቢያባብሉት ጨዌን ማለቱ አይቀርም ።

የጨጌ ከብት ፣ በየወገኑ ይከተት ።

የጫማ ጠጠርና የእንጀራ ልጅ ፣ እያደር መቆርቆሩ አይቀርም ።

የጫማ ጠጠርና የእንጀራ እናት ፣ እያደር መቆርቆሩ አይቀርም ።

የፈላ ጠጅ ፣ የደረሰ ልጅ ።

የፈረሰኛ ማቅ ለባሽ ፣ የቤት ትንባሆ ጎራሽ ።

የፈረሰኛ ጥለት ለባሽ ፣ የቤት ትምባሆ ጎራሽ ።

የፈረስ አልጋ ፣ የተሸበረ ዜጋ ።

የፈረንጅ አሽከር ፣ ነጭ ለባሽ ፣ ሳህን አመላላሽ ።

የፈሩት ይደርሳል ፣ የጠሉት ይወርሳል ።

የፈሰሰ ፣ አልታፈሰ ።

የፈሰሰ ውሃ አይታፈስ ።

የፈሲታ ፣ ተቆጢታ ።

የፈስ ማደናገሪያው ዳባ ።

የፈቷት ሚስት ፣ ያጠቡት ወጭት ፣ የወጡበት ቤት አንድ ነው ።

የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል ።

የፊተኛውን አሳረርሽ ቢሏት ፣ የሁዋለኛውን ጥሬ አወጣች ።

የፊት መሪ ፣ የሁዋላ ቀሪ ።

የፊት ምስጋና ፣ ለሁዋላ ሃሜት ያስቸግራል ።

የፊት እድፍ በመስታወት ፣ የሃጢአት እድፍ በካህናት ።

የፊት ክብት ፣ የእጅ ወረት ።

የፊት ወዳጅህን በምን ቀበርከው? በሻሽ ፤ የሁዋለኛው እንዳይሸሽ ።

የፊት የፊቱን አለ ጓያ ነቃይ ።

የፋቂ ልጅ ሰነፍ አንዱን ሳይፍቅ ፣ አንዱን ይዘፍቅ ።

የፋቂ ሰነፍ አንዱን ሳይፍቅ ፣ አንዱን ይዘፍቅ ።

የፋቂ ቆንጆ ቡድንነት አይታወውም ።

የፌጠ ብቅል ፣ የብሳና ጌሾ ፣ የተልባ አሻሮ ፣ ይህን ጠምቆ ለማነ የሰው ነገር ለማይ ሰማ ።

የፍቅር ጣእሙ ፣ በመሳለሙ ።

የፍየል ልጁን ፣ የሴባ እጁን ።

የፍየል ጅራት ከብርድ አያድን ፣ ብልት አይከድን ።

የፍየል ጅራት ከብርድ አያድን ፣ እፍረት አይከድን ።

የፍየል ጭራና የሰው ሀሳብ ፣ ሁልጊዜ ወደ ላይ ነው ።

የፍጅት ወራት ፣ እሳት በወንፊት ።

ያ በሬ ባላገደደ ፣ ያ በሬ ገደል ባልገባ ።

ያ በሬ ባገደደ ፣ ያ በሬ ገደል ገባ ።

ያህያ ልጅ ጥሎ ይረግጣል ፣ የፈረስ ልጅ ጥሎ ይደነግጣል ።

ያህያ ስጋ ፣ ካልጋ ሲሉት ካመድ ።

ያህያ ስጋ ውርደተኛ ፣ አልጋ ላይ ቢያኖሩት እመሬት ይተኛ ።

ያህያ ቀበጥ ፣ ከጅብ ጡት ይጣባል ።

ያህያ ባል ፥ ከጅብ አያስጥል ።

ያህያ እንግዳ ፥ የጅብ ራት ነው ።

ያህያ ውሀ ጠጭ ፥ ሳይታወቅ መጣጭ ።

ያህያ ፍለጋና የጥሬ ራት በግዜ ነው ።

ያለ የሚኖር ይመስላል ፥ የሞተ ያልነበረ ይመስላል ።

ያለ ይበዛል (አለወፍሮ)።

ያለህ ምዘዝ ፥ የሌለህ ፍዘዝ ።

ያለመከራ ፥ አይገኝም እንጀራ ።

ያለመከራ ፀጋ ፥ ያለ ድካም ዋጋ አይገኝም ።

ያለመጥረቢያ እንጨት ሰባሪ ፥ የቆማጣ ዘንግ ወርዋሪ ።

ያለሴት ምን ያደርጋል ቤት ።

ያለሴት ቤት ፥ ያለበሬ መሬት ።

ያለስራ መብል ፥ ያለ ዳኛ ውል ።

ያለስራ አይበላ እንጀራ ።

ያለስፍራው የተሰበረ ፥ ሲጠግኑት ያስቸግራል ።

ያለበሬ ፥ ምን ያደርጋል ገበሬ ።

ያለበት ይብላላበት ።

ያለበት ይጉላላበት ።

ያለባለቤቱ ፥ አይነድም እሳቱ ።

ያለአቻ ጋብቻ ፥ ቆይ ብቻ ቆይ ብቻ ።

ያለእዳው ዘማች ፥ ዋ ብሎ መቅረት ።

ያለከንፍ መብረር ፥ ያለ ስራ መክበር ።

ያለው ይምዘዝ ፣ የሌለው ይፍዘዝ ።

ያለው ይበላል ፣ የሌለው ያፈጣል ።

ያለውን ካልሰጡ ፣ በስም አይበሉ ።

ያለዘዴ ጋሻ ፣ እንቅብ ነው ።

ያለዝናብ ነጎዳ ፣ ያለብድር እዳ ።

ያለጊዜው የተወለደ ልጅ ፣ አባቱን ጥሎ እያቱን ያስረጅ ።

ያለጎረቤት ቡና ፣ ያለ ሙያ ዝና ።

ያለጎታ ደረባ ፣ ያለልብስ ካባ ።

ያለጎታ ደረባ ምንድነው ?

ያለጥርስ ቆሎ ፣ ያለ ጓድ አምባገር ።

ያለጨው በርበሬ ፣ ያለጥፈር በሬ ።

ያለፈቱ አይቆርስ ፣ ያለቤቱ አይወርስ ።

ያለፍርድ ማሰር ፣ በፈጣሪ ማማረር ።

ያለፍቅር ሰላም ፣ ያለ ደመና ዝናብ ።

ያለፍቅር ፀሎት ፣ ያለ እንጨት እሳት ።

ያሉሽን በሰማሽ ፣ ገበያ ባልወጣሽ ።

ያላረፈች ምላስ ፣ ሽማ ትልስ ።

ያላረፈች እግር ፣ ከዘንዶ ጉድጓድ ትገባለች ።

ያላሰብከውን አግኝ ፣ መረገምም ምርቃንም አይደል ።

ያላሳደጉት ውሻ ቤት ዘግተው ቢመቱት ዞሮ ይናከሳል ።

ያላባቱ ቢዛቁን ፣ አባክኖ ያባክን ።

ያላወቁ ፣ አለቁ ።

ያላዋቂ ቆራሽ ፣ ማእድ አበላሽ ።

ያላየ ልጅ ዳቦ ፍሪዳው ።

ያላዩት አገር አይናፍቅም ።

ያሏሟል ፣ ይተረጉሟል ።

ያልሞላ ተርፎ አይፈስም ።

ያልሞተና ያልተኛ ብዙ ይሰማል ።

ያልሰማ ጆሮ ፣ ከጎረቤት ያጣላል ።

ያልሰማ ጥኑ ነው ፣ ባልሽ ወዳጁ ነው ።

ያልሰጡት ተቀባይ ፣ ያልጠሩት አቤት ባይ ።

ያልሳሉት አይላጭ ፣ ያላዩት አይቆጭ ።

ያልቆረጠ እግብ አይደርስም ።

ያልበሉት እዳ ፣ ያልጠሩት እንግዳ ።

ያልበላ ሬሳ ፣ ያልለበሰ እንሰሳ ።

ያልበላ ዳኛ አያሟግት ፣ ያልጠጣ እንግዳ አያጫውት ።

ያልበላኝን ቢያከኝ ፣ አይገባኝ ።

ያልተማረ አይፀድቅ ፣ ያልተወቀረ አያደቅ ።

ያልተማረ ዋናተኛ ፣ ከዳኛ ፊት እንቢተኛ ።

ያልተረታ አይረታ ፣ ያልጠገበ አይማታ ።

ያልተሾመ አያዝ ፣ ያልቀሰሰ አያናዝዝ ።

ያልተቀጣ ልጅ ቢቆጡት ያለቅሳል ።

ያልተቀጣ ልጅ ፣ ያልታጠበ እጅ ።

ያልተነካ ግልግል ያውቃል ።

ያልተገላበጠ ያራል ።

ያልተገራ ፈረስ ፥ ይጥላል በደንደስ ።

ያልተፈተነ ወዳጅ ያልተተኰሰ ሽክላ ።

ያልታየ እንጂ ያልተሰማ ፥ ያልተደረገ እንጂ ያልተባለ ነገር የለም ።

ያልታደለ በሬዶ ከድንጋይ ላይ ያርፋል ።

ያልታደለ ከንፈር ሳይሳም ያረጃል ።

ያልታደለች ወፍ አይንዋ በጥቅምት ይጠፋል ።

ያልነበረ ያፈርሳል ፥ ቀዳዳ ያፈሳል ።

ያልወለደ አንጀት ጨካኝ ነው ።

ያልወለደ አይነሳ ፥ የሽምብራ ማሳ ።

ያልወለደ ፥ አጋድሞ አረደ ።

ያልወለዱ ሁሉ ፥ ጊደሮች ይባላሉ ።

ያልወለድኩት ልጅ አባባ ቢለኝ ፥ አፌን ዳባ ዳባ አለኝ ።

ያልዘሩት አይበቅልም ።

ያልዘራሁት በቀለብኝ ፥ ዱባ ያልኩት ቅል ሆነብኝ ።

ያልዘራውን የሚበላ ዝንጀሮ ነው ።

ያልገደለ ዘማች ፥ ያልወለደ አማች ።

ያልጋ ሴሰኛ ፥ ሶስት ያስተኛ ።

ያልጠረጠረ ፥ ተመነጠረ ።

ያልጠኑት መከሬ ፥ ያልሾሙት ፈታውራሪ ።

ያልጠሩት ሰርገኛ ፥ በትረኛ ።

ያልጫ ድንፋታ እንጀራ እስኪቀርብ ።

ያልፋል ፥ እስኪያልፍ ያለፋል ።

ያመል ትንሽ ፥ ይጥላል በጭራሽ ።

ያመነታ ፥ ተመታ ።

ያመኑት ሲከዳ ፥ ይቀላል እዳ ።

ያመኑት ፈረስ ፥ ጣለ በደንደስ ።

ያመጣሁት ውሻ ነከሰኝ ፥ ያነደደኩት እሳት ጠበሰኝ ።

ያመጣል አንበሴ ፥ ይበላል ኮሳሴ ።

ያማከሩት ዳኛ ያግዛል ፥ የመተሩበት እጅ ይወዛል ።

ያምራል ብለው ሰነብር ልጅ አይድሩም ።

ያምራል ብለው ከተናገሩት ፥ ይከፋል ብለው ያስቀሩት ።

ያምራል ብለው ከመናገር ፥ ይከፋል ብሎ መተው ።

ያምራል ብሎ ይሽልሟል ፥ ያውቃል ብሎ ይሾሟል ።

ያምሯል ፥ ይታደሏል ።

ያምና ጥኝ ፥ ዘንድሮም ድገመኝ ።

ያምናውን ዘንድሮ ፥ የአዋጁን በጆሮ ።

ያሞላቀቁት ልጅ ፥ አይሆንም ወዳጅ ።

ያሞሌ ጥጃ ፥ በወንዟ ትነፋ ።

ያረሮ ልጅ ጠለፋ ።

ያረሰ ፥ እንደልቡ ጎረሰ ።

ያረጀን ሹም ገባር ይከሰዋል ፥ ያረጀን ጅብ አህያ ይልሰዋል ።

ያራስ ከፋ መበለት ፥ ያዶጋ ከፋ እሳት ።

ያራሷን በርጉዟ ።

ያራቧን ገንፎ እርጉዟ ውጣ ሞተች ።

ያርጋጅ ፣ አናጋጅ ።

ያሰረ ይፈታል ፣ የሰጠ ይረታል ።

ያሰቡት አይገድም ፣ ጎኔን ላርገው ጋደም ።

ያላደግሁዋት ጥጃ ፣ አለችኝ በርግጫ ።

ያስታርቀኛል ሙተራ ፣ እያንዳንዱ እየኮራ ።

ያሽላል ያሉት ፣ ኩል አይን ያጠፋል ።

ያቀረቡልህን ጉረስ ፣ የተረፈህን መልስ ።

ያበደ ለኑሮው ፣ የፈረደ ለጉሮሮው ።

ያበደች ጋለሞታ ፣ እናቷን ትመታ ።

ያበጠው ይፈንዳ ።

ያባሆይ መቋሚያ ፣ ላዩ ባላ ታቹ ዱላ ።

ያባ ጎፍናኔ ቤቱ በሪድ ።

ያባቱን ቢሰጡት ሀይወቱ ፣ ያባቱን ቢነሱት ሞቱ ።

ያባት ልጅ የደንደስ ስጋ ።

ያባት ምርቃት ፣ አያስገባም ጥቃት ።

ያባቴ ሞቱን አይወዱ ፣ ረጃቱን አይሰዱ ።

ያባት ሲቀር ፣ ምሰሀ ቅበር ።

ያባት አገር ከሞት አያስጥልም ።

ያባት እርግማን ሲዳሩ ማልቀስ ።

ያባት እዳ ለልጅ ፣ ያፍንጫ እድፍ ለጅ ፣ የወፍጮ እዳ ለመጅ ።

ያባት ወርቅ ባለዝና ፣ እህል ለቀጠና ።

ያባት ያምራል ፣ የባእድ ያናግራል ።

ያባት ደግ ይደልላል ፣ ያባት ክፉ ለእንጀራ ልጅ ያደላል ።

ያባትህ ቤት ሲበዘበዝ አብረህ ዝረፍ ።

ያባትህና የናትህ ወገኖች ሲጣሉ ጥግህን ያዝ ።

ያባያ ልጅ ወዳቂ ፣ ያራኝ ልጅ አጥባቂ ።

ያባያ እናት አትታረድም ።

ያባያ ወንድሙ አይታረድም ።

ያባይ ምልክቱ አንደበቱ ፣ የገዳይ ምልክቱ ሽልማቱ ።

ያባይ እንባ አይታገድም ።

ያባይ ውሃ ተለያየ ሲሉት ተገናኘ ።

ያባይን እናት ፣ ውሃ ጠማት ።

ያብሮ አደግ ልብ በቁና ይሰፈራል ።

ያብዬን እከክ ፣ ወደ እምዬ ልክክ ።

ያናጢን ልጅ ጅብ በላው ፣ የላጭን ልጅ ቅማል ፈጀው ።

ያንበሳ ልመና ጋማ ይዞ ነው ።

ያንበሳ ልመና ጋማ ይዞ ፣ የቄስ ልመና እናዞ ።

ያንበሳ ማላጅ ጋማ ይዞ ፣ ጅብን መውጋት አህያን ተንዝንዞ ።

ያንበሳ ኮርዳዳና የጨዋ ልጅ ሞግዚት ከመሆን ይሰውርህ ።

ያንተን የሚመስል ፣ የኔም አለኝ ቁስል ።

ያንችን አትበይ ገንዘብ የለሽ ፣ የሰው አትበይ ምግባር የለሽ ።

ያንካሳ ልቡ ኢየሩሳሌም ።

ያንዱ በሬ ሲሞት ላንዱ አጋዘኑ ፣ ላንዱ ፍስሃው ላንዱ ሀዘኑ ።

ያንዱ ቤት ሲቃጠል ፣ ላንዱ ቋያው ነው ።

ያንዱ ቤት ሳይጠፋ ፣ ያንዱ ቤት አይለማ ።

ያንዱ ነገር ላንዱ የእንጀራ ልጁ ነው ።

ያንዱ አገር መልከኛ ላንዱ አገር ገባር ነው ።

ያንድ ሳም ወተት ፣ ያንድ እርሻ እሸት ።

ያንድ ሚስቱን ፣ የሺ ከብቱን ።

ያንድ ሰው ፍቅር ባንድ እጅ እንደማጨብጨብ ያለ ነው ።

ያንድ በሬ እሸት ፣ ያንድ ላም ወተት ።

ያንድ ቀን ስህተት ፣ የዘላለም ፀፀት ነው ።

ያንድዋ እለት ፣ አንድዋ ባልቴት ።

ያኖሩት እንቅርት ያገለግላል ።

ያኩራሩ ምሳ እራት ይሆነዋል ።

ያኮረፈ ፣ ልብሱን አራገፈ ።

ያኮረፈ ምሳው ራቱ ነው ።

ያወረደ መአቱን ፣ ያመጣ ምህረቱን ።

ያወቀ ተጠነቀቀ ፣ የዘነጋ ተነጠቀ ።

ያወቀ ተጠነቀቀ ፣ የዘነጋ ተወጋ ።

ያወቀ ተጠነቀቀ ፣ ያላወቀ ተነጠቀ ።

ያወቀ ፣ ናቀ ።

ያወቀ ዘለቀ ፣ ያላወቀ አለቀ ።

ያዋቂ ሴት ቤት ፣ አለው ውበት ።

ያዋቂ አጥሬ ፣ የእስራኤል ጣሬ ።

የአዋቂ አጥፊ ፣ የያመኛ ገዳፊ ።

ያዋጇን በጆሮ ፣ የእለቱን በቀጠሮ ።

ያውሬ ስጋ ለወሬ ።

ያውቃል ብሎ ይሾሟል ፣ ያምራል ብሎ ይሸልሟል ።

ያዛኸር ቤት ክርስቲያን ሳሚ ፣ ያጋፋሪ ራስጌ ቋሚ ።

ያየ ልናገር ቢል ፣ የሰማ ላውራ አለ ።

ያየ ቢሄድ ፣ የሰማ ይመጣል ።

ያየ ቢሄድ ፣ ያልሰማ ይመጣል ።

ያየ ይናገራል ፣ የተወለደ ይወርሳል ።

ያዩትን ቢያጡ ፣ ያላዩትን ይቀላውጡ ።

ያይን ጨንቋራ ሁሉ ያየዋል ።

ያይጥ ምስክሯ ፣ ድንቢጥ ።

ያይጥ ሞት ፣ የድመት ሰርግ ።

ያይጥ እርዳታ በጭራንፎ ያልቃል ።

ያይጥ ፋከራ ለመከራ ፣ ድመት ምን ሊበላ ።

ያይጦች ዝላይ ፣ ለነአቶ ውሮ ሲሳይ ።

ያደረገችውን ታስታውቅ ፣ ከደረቷ ትታጠቅ ።

ያደፈ በእንዶድ ፣ የጎለደፈ በሞረድ ።

ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይቀርም ።

ያዳኘ ውሻ ጠጉር ባፉ ፣ ብትር ትርፉ ።

ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ ።

ያገሩን ሰርዶ ያገሩ በሬ ይወጣዋል ።

ያገር ልማት ፥ የገበሬ ሀብት ።

ያገር ልጅ በምን ይመታል? በኩበት ፤ ያም እንዳይሄድ ፥ ያም እንዳይሞት ።

ያገር ልጅ ፥ የማር እጅ ።

ያገር እድር ፥ ለንጉስ ያስቸግር ።

ያገር እድር ፥ ጠም ያሳድር ።

ያገርህ ልጅ ብታገባት ሚስትህ ፥ ብትፈታት እህትህ ።

ያገርህ ዱር ፍራትን ያስወግድል እንጂ ከሞት አያድንም ።

ያገባሽ ይፈታሻል ፥ ይብላኝ ለወለደሽ ።

ያገኘ ከራሱ ፥ ያጣ ከዋሱ ።

ያጓኑት ድንጋይ ተመልሶ ራስን ።

ያጣ ሰው ያገኘ አይመስለውም ።

ያጥንት ፍላጭ ፥ የስጋ ቁራጭ ።

ያፍ አማኝ አደረገኝ ለማኝ ።

ያፍ ወለምታ በቅቤ አይታሽም ።

ያፍ ዘመድ ፥ በመንገድም አይገድ ።

ያፍላ የለው ቀርፋፋ ።

ይህ ሁሉ ከርከሬሻ ፥ ባንቺ የተነሳ ።

ይህ ሁሉ ጠባሳ ፥ ባንቺ የተነሳ ።

ይህ አንበሳ ፥ ደምደም አገሳ ።

ይህ ከርከሬሻ ፥ ዳቦዬን ለማንሻ ።

ይህን ብስጥ ፥ ምን እውጥ ።

ይህን ፈርቼ ፥ ደጄን በቀን ዘግቼ ።

ይሆናል ብዬ ጎሽ ጠመድኩ ፡ የማይሆን ቢሆን ፊትቹ ሰደድኩ ።

ይሆን ቢሆን ፡ ዝሆን ይበላ ቢሆን ።

ይሉ አይሉ ፡ የት አለ ቅሉ ።

ይሉኝን ብትሰሚ ፡ ጎንደር ላይ ከረሚ ።

ይሉኝ አይል ውሽማ ፡ ዶሮ ሲጮህ ይማለላል ።

ይሉኝ አይል ፡ የሁዋላውን አያይ ።

ይሉኝ አይል ፀሀፊ ከሙሴ ይገድፋል ።

ይሉኝታ ፡ የራስ አሊን ቤት የፈታ ።

ይሉኝታና መጠቀም ፡ አንድ ላይ አይገኝም ።

ይመስክረዋል ለነፍሱ ፡ ይፈተፍተዋል ለከርሱ ።

ይመታሉ የሚጠሉ ይመስል ፡ ይስማሉ የሚወዱ ይመስል ።

ይሙት የገደለ ፡ ይካስ የበደለ ።

ይማሩኝ እያልክ ከምትታማበት አትገኝ ።

ይምሰል አይምሰል ፡ የጠይብ እጁ ተከሰል ።

ይስጡኝ ብሎ ከሰጠ ፡ ቆጥቦ የበላ በለጠ ።

ይሰጣል መስሎ ይሸጣል ።

ይስበረኝ ይሰንጥረኝ የሚሉ ፡ የሰውን ልብ ሊሰብሩ ።

ይቅር ለእግዜር ፡ ወድቆ እማይሰበር ።

ይቅር ለእግዜር ፡ ወድቆ አይሰበር ፡ ሞቶ አይቀር ።

ይቅደም ደግነት ፡ ይከተል ቸርነት ።

ይበላ እንደቤቱ ፡ ይሰራ እንደ ጉልበቱ ።

ይበላ እንደ ቤቱ ፡ ይሰራ እንደ ጎረቤቱ ።

ይበላው ካጣ ፣ ይበላበት ያጣ ።

ይበጃል ያሉት መድሀኒት አይን አጠፋ ።

ይበጃል ያሉት ኩል አይን አጠፋ ።

ይብራና ይብራ ፣ ተጣሉ በሰው ሽንብራ ።

ይታደሏል እንጂ ይታገሏል ?

ይች ባቄላ ያደረች እንደሆን አትቆረጠምም ።

## - ደ -

ደሀና ሲታጣ ፣ ይመለመላል ጎባጣ ።

ደሀና ወገን ያጣ ፣ ወየው ያለበት ጣጣ ።

ደሀና ጦር ያለው ፣ ለግምብ ይሞክረው ።

ደመና ለዝናብ ፣ ድግስ ለሆዳም ።

ደመና በሰማይ ፣ የጨዋ ልጅ በአደባባይ ።

ደመና የጨበጠ ፣ ሰማይ የቧጠጠ የለም ።

ደም ቢያለቅሱ ፣ ድንጋይ ቢነክሱ ።

ደም ተቀብቶ ዝንብ አይፈሩም ።

ደም ተበክለሀ ዝንብን አትጥላ ።

ደሞዙ ስንዴ ፣ ስራው የምን ግዴ ።

ደሞዝ ያጣ ሎሌ ፣ ይኮበልላል በሃምሌ ።

ደሞዝተኛ ፣ እርፈሀ አትተኛ ።

ደረስሁ ልጅ ፣ ፈላሁ ጠጅ ።

ደረቅ ይቀመጠላል ፣ እርጥብ ይነብጣል ።